社会開発調査部報告書

No. 21

# በ11 ከተሞች የመጠጥ ውኃና ሳኒቴሽን ጥናት
# የንፅህና አጠባበቅ ትምህርት
# ማስተማሪያ ዘዴዎች መመሪያ

## በጃፓን ዓለም አቀፍ ትብብር ድርጅት
## እና በውኃ ሀብት ሚኒስቴር
## ትብብር የተዘጋጀ


## ሳንዩ የአማካሪ ድርጅት
## ኪዩዋ የምሕንድስና አማካሪ ድርጅት


JICA LIBRARY
J 1130186 [8]

ታህሣሥ 1988
በመጠጥ ውኃና ፍሳሽ
አገልግሎት መምሪያ
አዲስ አበባ

RY

SSS
J R
96-028

# በ11 ከተሞች የመጠጥ ውኃና ሳኒቴሽን ጥናት
# የንፅህና አጠባበቅ ትምህርት
# ማስተማሪያ ዘዴዎች መመሪያ


## በጃፓን ዓለም አቀፍ ትብብር ድርጅት
## እና በውኃ ሀብት ሚኒስቴር
## ትብብር የተዘጋጀ

## ሳንዩ የአማካሪ ድርጅት
## ኪዩዋ የምሕንድስና አማካሪ ድርጅት



ታህሣሥ 1988
በመጠጥ ውኃና ፍሳሽ
አገልግሎት መምሪያ
አዲስ አበባ

1130186 (8)

## መግቢያ

ይህ የንፅህና አጠባበቅ ማስተማሪያ ዘዴዎች መመሪያ የተዘጋጀው በ11 ከተሞች (ዱብቲ፣ ሚሌ፣ ባቲ፣ ደብረ ታቦር፣ ንፋስ መውጫ፣ ወረታ፣ አይከል፣ ቻግኒ፣ ቡሬ፣ ብቸና፣ ደጀን) የመጣ ውኃና የሳኒቴሽን ጥናት ላይ በመመርኮዝ ነው። ከዚህ ቀደም በርካታ የንፅህና አጠባበቅ ማስተማሪያ መጽሐፍት በተለያዩ ድርጅቶች የታተሙ ሲሆን ይህ መመሪያ ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት በአብዛኛው ትኩረት ያደረገው ትምህርቱን ለማስተላለፍ በሚያመቹ ዘዴዎች ላይ ሲሆን በተለይም ሕብረተሰቡን በይበልጥ ሊያሳትፉ በሚችሉ መንገዶች ላይ ነው። ለዚህም በአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ በተለይም በ11 ከተሞች የሚገኘውን ሕብረተሰብ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

ይህ የሕብረተሰብ ተሳትፎ አደራጆች እንዲገለገሉበት ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን እንዲሁም ከጤና ባለሙያዎች፣ ከትምህርት ቤቶች፣ ከኃይማኖት ድርጅቶችና ከተለያዩ የጤናና የአካባቢ ንፅህና ኮሚቴዎች ጋር በቅንጅት ለመስራት ያገለግላል። ለአሰልጣኞችም እንደ ማሰልጠኛ ሊሆን ይችላል።

በዚህ መመሪያ ውስጥ ለየት ያሉ አዳዲስ ገላጭ ምስሎችን ለማቅረብ ተሞክሯል። በምሳሌዎቹ ላይ የሚታዩት የሰዎች አለባበስ እና የመሳሰሉት የሚያመለክቱት በአስሩ እንዱ ከተሞች በአብዛኛው የሚገኘውን የደገኛውን ኅብረተሰብ ባህል ነው። ነገር ግን እነዚህ ምሳሌዎች በአካባቢው በተግባር ያልተፈተኑ ስለሆነ ይህ መመሪያ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ሙከራ ተደርጎበት አስፈላጊው ማስተካከያ ሊደረግ ይገባል። ይህን መመሪያ ማንኛውም የመስክ ሠራተኛ ሊገለገልበት የሚችል ሲሆን ዘዴዎቹንም ሆነ ምሳሌዎቹን ከየአባቢው ሁኔታ ጋር በማዛመድ መጠቀም ይቻላል።

በተጨማሪም በዚህ መመሪያ ውስጥ ከኅብረተሰቡ ጋር በቀላሉ ለመገናኘት፣ አስፈላጊ መረጃዎችን ከኅብረተሰቡ ለማግኘትና እንዲሁም ጠቃሚ ሀሳቦችን ወደ ኅብረተሰቡ (ለአዋቂዎችም ሆነ ለልጆች) እንዴት ማስተላለፍ እንደሚቻል የሚጠቀሙ ዘዴዎችን ለማሳየት ተሞክሯል። እንዲሁም በንፅህና አጠባበቅ ትምህርት ላይ እየተሳተፉ ያሉ ድርጅቶችን ዝርዝርና ለዚህ ትምህርት አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ የማስተማሪያ መጽሐፍት ዝርዝር አካቷል።

# ማውጫ

ገፅ


መግቢያ..........................................................................

1. ከኀብረተሰቡ ጋር መቀራረብ. ........................................ 1

2. የሕብረተሰቡን ሁኔታ ማወቅ. ........................................ 4

2ሀ. የጋራ ውይይት. ........................................ 9
2ለ. ድራማ /አጭር ትያትር/ ........................................ 9
2ሐ. በስዕላዊ ቻርቶች መምረጥ. ........................................ 11
2መ. የአካባቢያቸውን አቀማመጥ በጋራ መሣል. ........................................ 14
2ሠ. ገላጭ ስዕሎች (ፖስተሮች) ........................................ 17
2ረ. የኀብረተሰቡን የኢኮኖሚ አቋም መለየት. ........................................ 21

3. የመረጃ አጠቃቀም. ........................................ 21

4. የመማሪያ ዘዴዎች. ........................................ 26

4ሀ. የማሰላሰል ዘዴ. ........................................ 27
4ለ. የጎልማሳ-ጎልማሳ እና የልጅ-የጎልማሳ መማማር. ........................................ 35

5. የአካባቢ ንፅህና ትምህርት ተግባራት (ለትናንሽ ቡድኖች) ........................................ 35

5ሀ. የመተላለፊያ መንገዶች. ........................................ 36
5ለ. ድራማ በመጠቀም (ሀ) ........................................ 40
5ሐ. ድራማ በመጠቀም (ለ) ........................................ 41
5መ. ጤነኛ ሕፃን........................................ 42
5ሠ. የተቅማጥ በሽታ ሕክምና. ........................................ 44
5ረ. የኦ.አር.ኤስ አዘገጃጀትና አቀማመጥ (ጨዋታ) ........................................ 46
5ሰ. ሦስት ቦታ ካርዶችን መለየት. ........................................ 49
5ሸ. የችግር ሁኔታዎች. ........................................ 50
5ቀ. የቤቶች ማና........................................ 52
5በ. በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተደገፈ ጥናት. ........................................ 54
5ተ. ታሪኮችን መጠቀም. ........................................ 56

**ገፅ**


6. የንፅህና ትምህርት እንቅስቃሴ - ትላልቅ ቡድን. .................... 58

6ሀ. ፊልምና ቪዲዮ በመጠቀም. .................... 58
6ለ. የመንገድ ላይ ትርዒት መጠቀም (በድራማ መልክና አሻንጉሊቶች በማሳየት) .................... 59

7. ልጅ-ለልጅ ዓይነት አቀራረብ. .................... 65

8. የሁኔታዎችን ለውጥ መቆጣጠር. .................... 67

8ሀ. ራስን መመዘኛ ቅጽ (የመገምገሚያና የመከታተያ ቅፅ) .................... 69

9. በኢትዮጵያ ውስጥ በንፅህና አጠባበቅ ትምህርት ላይ የሚሳተፉ ድርጅቶች. .................... 71

10. ሌሎች ጠቃሚ ፅሑፎች. .................... 72

ይህንን መመሪያ ለማዘጋጀት እንደመንደርደሪያ የተጠቀምንባቸው ፅሑፎች. .................... 73

ሌሎች ለምሳሌ የሚሆኑ ስዕሎች. .................... 75

## 1. <u>ከኅብረተሰቡ ጋር መቀራረብ</u>

የንፅህና አጠባበቅ ትምህርትን ወደ ኅብረተሰቡ ከማስተላለፋችን በፊት በቅድሚያ የአካባቢውን ባለሥልጣናትና ሽማግሌዎች በመቅረብ ትምህርቱ በአካባቢው ኅብረተሰብ ዘንድ የሚፈለግና የማይፈለግ መሆኑን፣ አስፈላጊው ዕርዳታ የሚገኝ መሆኑንና ትምህርቱን ለማካሄድ ፍቃድ መኖሩን በቅድሚያ ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የአካባቢው ሽማግሌዎችና ባለሥልጣናት ሀሳባቸውንና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችካሉ ያለ ምንም ጣልቃ ገብነት በነፃነት እንዲናገሩ መገፋፋት ያስፈልጋል። በትምህርቱ ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቅራኔዎች ካሉ በቅድሚያ መታወቅ አለባቸው።

ትምህርቱን ለመስጠት ሲታቀድ ከዚህ የሚከተሉትን ነጥቦች በጥንቃቄ መከተል ይገባል።

- በቅድሚያ የአካባቢውን ሽማግሌዎችና ባለሥልጣናት ፍቃድ ማግኘት። የቅድሚያ ትኩረት ሊሻ የሚገባው ጉዳይ ካላቸው ይህን ማወቅና ለሚያቀርቧቸው አስተያየቶች ተገቢውን አክብሮት በመስጠት ለትምህርቱ መሳካት የእነሱ ሀሳብ ዋና ቁልፍ መሆኑን በመግለፅ ዕርዳታውንና ፍቃዳቸውን ማግኘት ያስፈልጋል።

- ግልፅ በሆነ መንገድና ምንም ነገር ባለመደበቅ ምን ለመስራት እንደተፈለገ ትህትና በተሞላበት መንገድ ማስረዳት፣

- ትምህርቱን መስጠት በሚቻልባቸው መንገዶች ላይ የአካባቢው ሽማግሌዎችና ባለሥልጣናት ሰፊ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ፣

- የሕብረተሰቡን ችግሮች ለማቃለል የተላከን ዓይነት መስለን በኅብረተሰቡ መታየት የለብንም። ነገር ግን የትምህርቱን ዕቅድ አፈጻጸምና ክትትል በተመለከተ ከኅብረተሰቡ ጋር በጋራ ለማከናወን የተዘጋጀን መሆናችንን ኅብረተሰቡን ማሳመን ይኖርብናል።

- ወደ ኅብረተሰቡ ውስጥ ገብተን ሥራችንን ከመጀመራችን በፊት በቅድሚያ ውይይቱን ለማካሄድ እንደምንፈልግ ከአካባቢው ባለሥልጣናትና ሽማግሌዎች ጋር ስምምነት ላይ መድረስ ይኖርበታል። በአካባቢው ታዋቂ የሆኑና ጠቃሚ ሀሳቦችን ሊሰጡ የሚችሉ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን ማነጋገር ያስፈልጋል። በአካባቢው ከሚገኙ የጤና ባለሙያዎች፣ የልማት ሠራተኞች፣ መምህራን፣ የሴቶች ተወካዮች፣ የልምድ አዋላጆች እና ከመሳሰሉት ጋር በመነጋገር በምን ዓይነት መንገድ፣ ከማን ጋር፣ መቼና የት ትምህርቱን ማካሄድ እንደሚቻል ጠቃሚ ሀሳቦችን ማግኘት ይቻላል።

- ከሁሉም በላይ ልናስተውለው የሚገባን ጉዳይ የእኛ ኃላፊነት ኅብረተሰቡ ያልተቀበለውንና ያልፈለገውን ለውጥ ለማምጣት ሳይሆን በተቃራኒው ኅብረተሰቡ የተቀበለውንና የፈለገውን ለውጥ በኅብረተሰቡ በራሱ ሊመጣ እንደሚችል ከኅብረተሰቡ ጋር አብሮ ለመስራት ነው።

- የሴቶችን ሀሳብ ማወቅ። በመጠጥ ውኃና በአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ እንቅስቃሴ ላይ የሴቶች ድርሻ ከሁሉም በላይ ከፍተኛ ስለሆነ የሴቶች አመለካከት ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ይህ ጥናት በተካሄደባቸው (አሥራ አንድ) 11 ከተሞች የውኃ አቅርቦትና አጠቃቀም በአብዛኛው የሴቶች ድርሻ ነው። በጤናና በአካባቢ ንፅህና ረገድ በእያንዳንዱ ቤተሰብ ውስጥ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት ሴቶች የሚኖራቸው ድርሻ ከየትኛውም የኅብረተሰብ ክፍል የበለጠ ነው። ስለዚህ ይህ የአካባቢ ንፅህና ትምህርት ግቡን እንዲመታ ከየትኛውም የኅብረተሰብ ክፍል በተለየ መልኩ በሴቶች ላይ ዋንኛ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል።

ማንኛውም ኅብረተሰብ የራሱ የሆነ ጠቃሚ ዕውቀት፣ አመለካከት፣ የሙያ ችሎታ፣ የጠለቀ ግንዛቤና ሀብት አለው። ስለዚህ የልማት ሠራተኛም ይሁን የኅብረተሰብ ተሳትፎ አደራጅ ሠራተኛ ዋንኛ ተግባር ኅብረተሰቡ እነዚህን ሀብቶች ጠቀሜታ ባለው ተግባር ላይ እንዲያውል ማድረግ ነው። ለዚህ ደግሞ ከሕዝቡ ጋር እጅ ለእጅ ሆኖ መሥራት ያስፈልጋል። ኅብረተሰቡ በራሱ የመተማመን ስሜት እንዲኖረው፣ በራሱ ጉዳይ ላይ ውሳኔ የመስጠት እና ለራሱ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን በራሱ አቅምና ጉልበት የመሥራት ልምድ እንዲያዳብር ማድረግ ያስፈልጋል። ሰዎች ምን እንደሚሠሩና እንዴት እንደሚሰሩ ሁልጊዜ የሚነገራቸው ከሆነ ጥገኛ የመሆን ባህሪ ይኖራቸዋል። ኅብረተሰቡ ለገጠመው ችግር መፍትሔ እንዲሰጠው በሚጠይቅበት ጊዜ መልስ ለመስጠት ከመቻኮል ኅብረተሰቡ በራሱ ለችግሮቹ መፍትሔ እንዲፈልግ ማበረታታት ያስፈልጋል። አንድ ሰው ብቻውን መፍትሔ ለማግኘት ሊከብደው ይችላል ነገር ግን በጋራ ብዙ አማራጮች ሊገኙ ይችላሉ።



## 2. <u>የሕብረተሰቡን ሁኔታ ማወቅ</u>

ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር ከተደረጉት ስብሰባዎችና ውይይቶች እንዲሁም ከዚህ ቀደም ስለ አካባቢው ከተጠናከሩ ዘገባዎች አንዳንድ ጠቃሚ መረጃዎችን ማግኘት ይቻላል።

የአንድን አካባቢ ኅብረተሰብ ሁኔታ ለመረዳት የሚያስችሉ የጥናት መሥፈርቶች ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል። ለእነዚህ ለተዘረዘሩት መሥፈርቶች ሙሉ በሙሉ ከመጀመሪያው መልስ ማግኘት ቢያስቸግርም ወደ ኅብረተሰቡ እየቀረብን በሄድን ቁጥር አብዛኛዎቹን መረጃዎች ማግኘት ይቻላል። መረጃ መሰብሰብ ዕቅድ ማውጣትና ግምገማ ማድረግ በአንድ በተወሰነ ወቅት የሚጠናቀቁ ሳይሆን ቀጣይነት ያላቸው ሥራዎች ናቸው። የሚሰበሰበውም መረጃ በዕድሜና በፆታ ተለይቶ መቀመጥ ይኖርበታል።

የሕዝብ ብዛት፣

- የሕዝብ ብዛት እንቅስቃሴና የሕዝብ ዕድገት፣
- የቤተሰብ ብዛትና አባላት ዓይነት (የቤቱ አባወራ ወንድ/ሴት በመለየት)፣
- የቤተሰቡ የገቢ ሁኔታ፣

ጤና፣

- ዋነኛ የጤና ችግሮች፣
- በውኃና በንፅህና ጉድለት ምክንያት ስለሚመጡ በሽታዎች፣
- የበሽታዎች ሥርጭት (በየወቅቱ)፣
- የበሽታዎቹ ምክንያቶች ይሆናሉ ብሎ ሕዝቡ የሚያምንባቸው ነገሮች፣
- የጤና አገልግሎት መስጫ ድርጅቶች ብዛትና ሁኔታ፣
- የጤና ባለሙያዎች ብዛት፣

**የውኃ ስርጭትና የአጠቃቀም ልምድ፣**

- በይበልጥ የሚጠቀሙባቸውና የሚፈልጓቸው የውኃ መገኛ ዓይነቶች በአጠቃቀም፣ /ለምሳሌ ለመጠጥ፣ ለገላ መታጠቢያ፣ ለልብስ ማጠቢያ ወዘተ... በመለየት/፣

- የውኃው መገኛ ርቀትና ውኃውን በቀላሉ የማግኘትና ያለማግኘት ሁኔታ፣

- የውኃው መገኛ ዓመቱን ሙሉ አገልግሎት መስጠቱን፣

- የውኃ አቫቫጥና ዋጋው፣

- የተፈለገውን ያህል ውኃ ማግኘት መቻልና አለመቻል ውኃው ለተደጋጋሚ አገልግሎት ይውላል? /ለምሳሌ እጅ የታጠበበትን ውኃ ለቤት መወልወያ ማድረግና የመሳሰሉት/፣

- ለውኃ መቅጃና ማጠራቀሚያነት የሚገለገሉባቸው ዕቃዎች ዓይነት፣

- ውኃውን በሚቀዱበትና በሚያጓጉዙበት ጊዜ ውኃውን ሊበክሉ የሚችሉ ሁኔታዎች ለምሳሌ የውኃ መቅጃው ክዳን ንፅህና ወዘተ...፣

- ውኃው ቤት ውስጥ በምን ይቀመጣል፣ አጠቃቀሙስ ለምሳሌ ከማጠራቀሚያው የሚቀዳበት ዕቃ እንዴት ይቀመጣል፣

- የውኃው መገኛ አካባቢ ለብክለት የተጋለጠ ነው ወይስ አይደለም? ለምሳሌ በአቅራቢያው ልብስ ይታጠባል? ለከብቶች አዳሪ የተጋለጠ ነው? ወዘተ...

- ውኃውን ለማጣራትና ብክለቱን ለመቆጣጠር በአካባቢው የሚደረገው ጥንቃቄ።

**የንፅህና አጠባበቅና የኅብረተሰቡ ግንዛቤ፣**

- የመፀዳጃ ቤት አጠቃቀም ለወንድ ለሴት ለልጆች ወዘተ... ለመጠቀምም ሆነ በሚጠቀሙበት ጊዜ የሚያጋጥማቸው ችግሮች ካሉ፣

- ዓይነ ምድር ከወጣ ወይም ከተፀዳዱ በኋላ ለዕዳት በምን ይጠቀማሉ /ወረቀት፣ ውኃ፣ ወዘተ.../፣

- ተፀዳድተው ሲመለሱ እጃቸውን በምን ይታጠባሉ በሣሙና ወይስ ሌላ፣

- መፀዳጃ ቤት ካላቸው ለገላ መታጠቢያ ይገለገሉበታል?

- መፀዳጃ ቤቱን ማን ያፀዳዋል፣ ይጠግነዋል፣

- መፀዳጃ ቤት ለመጠቀም/ለመሥራት በባሕልም ሆነ በአካባቢ ልማድ የሚከለክሉ ሁኔታዎች ይኖራሉ?

- መፀዳጃ ቤትን ለሴትም ሆነ ለወንድ በጋራ ለመጠቀም የሚያግዱ ሁኔታዎች አሉ/የሉም

- ልብስም ሆነ ዕቃ የታጠበበት ውኃ ወዴት ይደፋል፣

- ሣሙናን ለምን ለምን አገልግሎት እንደሚጠቀሙና ሁል ጊዜ እንደሚኖራቸው፣ እንደማይኖራቸው፣

- ምግብ እንዴት ይቀመጣል፣ ለምን ያህል ጊዜ ይቀመጣል፣

- ምግብ በሚዘጋጅበት ጊዜ የሚደረግ ጥንቃቄና ንፅህናው ምን ይመስላል፣

- የተሻሻሉ የንፅህና ዘዴዎችን ለመጠቀም የሚያግዱ ምክንያቶች ምንድናቸው?

**የትምህርት እንቅስቃሴ፣**

- የትምህርት ደረጃ፣

- ማንበብ መጻፍ የሚችል/የማይችል በመለየት፣

- የአስተማሪ ብዛት፣ በየትምህርት ቤቱ የሚገኙ የተማሪዎች ብዛትና ሁልጊዜ አዘውትረው ወደ ትምህርት ቤት የሚመጡትን በመለየት፣

- በተከታታይም ሆነ አልፎ አልፎ የሚሰጥ የጤና ትምህርት፣

- የመገናኛ ብዙኃን ተጠቃሚ ብዛት፣

**የአካባቢ ማኅበራትና የሕዝቡ ተሣትፎ፣**

- በአካባቢው የሚገኙ ዋና ዋና ማኅበራትና የአባላት ብዛት ሁኔታ፣
- የአካባቢው ባለሥልጣናት በዖታ፣
- በሕዝቡ ተሳትፎ ላይ ተፅዕኖ ማሳደር የሚችሉ በአካባቢው የሚገኙ የፖለቲካና የማኅበራዊ ቡድኖች እንዲሁም ታዋቂ ግለሰቦች፣
- ከዚህ ቀደም በተደረጉ የውኃ፣ የአካባቢ ንፅህና ወይም የልማት እንቅስቃሴዎች ላይ ሕዝቡ ያሳየው ትብብርና ተሳትፎ፣
- በኅብረተሰቡም ሆነ በቤተሰብ ውስጥ ውሳኔ የመስጠትና የማስተዳደር ኃላፊነት በአብዛኛው እንዴትና በማን ይፈጸማል፣

**የመተዳደሪያ ሥራ፣**

- ዋንኛ የአካባቢው ኅብረተሰብ የገቢ ማግኛ እንቅስቃሴዎች፣
- የኅብረተሰቡ ዋና ዋና የገቢ ምንጮች፣

**የሕዝቡ ፍላጎት/ደረጃ፣**

- ንፅህናና የመጠጥ ውኃን በተመለከተ መሻሻሎች እንዲደረጉ የሕዝቡ ፍላጎት ምን ደረጃ ላይ ይገኛል፣
- ለውጦችንና መሻሻልን ለማምጣት በሚደረገው ጥረት ሕዝቡን ለመምራትና ለማስተባበር የተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች ሊያሳዩ የሚችሉት ትብብር፣

**የአካባቢው አቀማመጥና አሠፋፈር**

- የቤቶች ዓይነትና ይዞታቸው /አዳዲስ፣ አሮጌ በጥላን የተሠሩ ወዘተ.../፣
- ለቤቶቹ ግንባታ የሚጠቀሙባቸው ቁሳቁሶች ዓይነት፣
- አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙት የውኃና የአካባቢ ንፅህና ተቋሞች (የሕዝብ/የሠፈር፣ የግል)፣
- የሱቅ፣ የገበያና የቢሮ አገልግሎት፣
- የሀይማኖት ተቋሞች፣

**ገንዘብ ለመክፈል አቅምና ፍላጎት**

- የመሬትና የመኖሪያ ቤት ባለቤትነት ሁኔታ፣
- የገቢ መጠን፣
- የወጪዎች ዓይነትና መጠን፣
- ገንዘብ የመበደርና የማጠራቀም ልማድ፣

**በአካባቢው አስፈላጊው የሰው ኃይልና የግንባታ ቁሳቁሶች መኖር**

- የግንባታ ቁሳቁሶች በአካባቢው መኖር፣
- የሠለጠነና ያልሠለጠነ የሰው ኃይል በአካባቢው መገኘት፣
- ወዘተ...፣

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት መረጃዎች ለማንኛውም የልማት ሠራተኛ ጠቀሜታ አላቸው። ኅብረተሰቡን በማሳተፍ መረጃዎችን መሰብሰብ ጠቃሚ የሆኑ ድብቅ መረጃዎችን ከማስገኘቱም ባሻገር ለቀጣዩ ሥራ ተገቢውን ትብብርና ግምገማ ለማግኘት ያስችላል። የዚህ ዘዴ ዓላማ ቀለል ባለ ሁኔታ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሲሆን ከዚህም ባሻገር ኅብረተሰቡ በቀላሉ እንዲረዳውና እንዲያውቀው ነው።

ከዚህ የሚከተሉት ዘዴዎች ደግሞ ኅብረተሰቡን በተለያዩ አነስተኛ ቡድኖች በመክፈል መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚቻልባቸውን መንገዶች ያመለክታሉ።


## 2ሀ. <u>የጋራ ውይይት</u>

በዚህ የውይይት ዘዴ የአብዛኛውን ኅብረተሰብ አመለካከት ለመረዳት የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም (ለምሳሌ በሠፈር፣ በፆታ፣ በገቢ መጠን ወዘተ...) ኅብረተሰቡን በትናንሽ ቡድኖች በመክፈል ማወያየት። በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን ሴቶች አመለካከት ምን እንደሚመስል ማወቅ፣ የገቢ መጠናቸው ከፍተኛም ሆነ አነስተኛ የሆኑትን በመለየት፣ አቅመ ደካማ የሆኑትንና እንዲሁም ሁሉንም የሕብረተሰቡን ክፍሎች ማወያየት ያስፈልጋል።

የጋራ ውይይቱን ለማካሄድ የሚመሠረቱት ቡድኖች አባላቶች በተቻለ መጠን በተመሳሳይ የኑሮ ደረጃና ተመሳሳይ እንቅስቃሴ ያላቸው ቢሆኑ ይመረጣል። የዚህ ውይይት ዋና ዓላማ ሕዝቡ በጉዳዩ ላይ ሰፋ ባለ መልኩ በፈለገው ሁኔታ እንዲሳተፍ ስለሆነ ጠንከር ያሉ የስብሰባ ሥነ ሥርዓቶች እንዲጠበቁ አያስፈልግም። የማስተማሪያ መድረክም ስላልሆነ ዋናው ተሳታፊ ሕዝቡ መሆን አለበት። ውይይቱም ሕዝቡ በፈለገው መንገድ የሚካሄድ ስለሆነ ቀደም ተብለው የተቀረፁ የውይይት አካሄዶችን አጀንዳዎችን አጥብቆ መከተል አያስፈልግም።

## 2ለ. <u>ድራማ /አጭር ትያትር/</u>

ይህ ድራማ የሚዘጋጀው በኅብረተሰቡ በራሱ ሲሆን በተለይም በአካባቢው በሚገኙ ወጣቶችና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ቢዘጋጅ የበለጠ ቀላል ይሆናል። ድራማው በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚታዩትን ልምዶችንና ባህሪያትን እንዲያካትት ለማድረግ በቅድሚያ ከኅብረተሰቡ ጋር በጋራ ችግሮቻቸው ላይ ውይይት ማድረግ። ከዚህም በመቀጠል ድራማውን ለማዘጋጀት ብቃት የሚኖራቸውን አባላቶች ከኅብረተሰቡ እንዲሁም ከትምህርት ቤቶች ወዘተ... በመነጋገር እስከ ከ20 እስከ 30 የሚደርሱ አባላቶችን መምረጥ።



- የተመረጡትን አባላቶች ከ5 እስከ 8 አባላት ባለቸው ከ3 እስከ 4 በሚደርሱ ትንንሽ ቡድኖች መከፋፈል፣

- እያንዳንዱ ቡድን ከ5-10 ደቂቃ ያህል በአካባቢው ያሉትን ችግሮች በዝርዝር እንዲገልፅ ማድረግ፣

- በመቀጠልም ከዘረዘሯቸው ችግሮች ይበልጥ አሳሳቢ የሆኑትን አንዳንድ አርዕስተ-ጉዳዮች እንዲመርጡ በማድረግ ይህንን በድራማ መልክ ለኅብረተሰቡ ለማቅረብ እንዴት እንደሚችሉ ማወያየት። የእያንዳንዱ የድራማ ጊዜ ከ5 ደቂቃ ባይበልጥ ይመረጣል። የድራማውም ዓላማ ሕዝቡን ለማወያየት እና ለማነቃቃት እንጂ እንደ መደበኛ የድራማ አሠራር ብዙ ውጣ ውረድና ሙያ የሚያስፈልገው አይደለም።

- ድራማው ለኅብረተሰቡ ከመቅረቡ በፊት አዘጋጆቹ ለተወሰነ ጊዜ በመደጋገም እንዲለማመዱት ማድረግና አንዱ ቡድን ለሌላው ቡድን እንዲያሳየው በማድረግ እርስ በራሳቸው እንዲተራረሙ ማበረታታት።

- ድራማው ለሕዝብ በሚቀርብበት ጊዜ በተቻለ መጠን ሕዝቡ መልዕክቱን ሊያደምጥ የሚችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት። ድራማውም ከአንድ በላይ ከሆነ በመሀሉ ብዙ ጊዜ ሳይባክን በየተራ ማሳየት ወይም እያንዳንዱ ድራማ ካለቀ በኋላ ከሕዝቡ ጋር አጠር ያለ ውይይት ማድረግ አስፈላጊ መሆን አለመሆኑን በቅድሚያ ተነጋግሮ መወሰን።

- በመጨረሻም የድራማው ጊዜ እንደተጠናቀቀ የሕዝቡን መንፈስ በማየት አጠር ያለ ውይይት ለማድረግ መሞከር።

## 2ሐ. <u>በስዕላዊ ቻርቶች መምረጥ</u>

የአብዛኛውን ኅብረተሰብ የግልና የአካባቢ ንፅህና ልምድ እንዲሁም የመጠጥ ውኃ አጠቃቀም ወዘተ... የመሳሰሉትን እንቅስቃሴዎች ስዕላዊ በሆነ መንገድ በማስቀመጥ እያንዳንዱ የኅብረተሰብ አባል የአጠቃቀም ዓይነቱንና ልማዱን እንዲያሳይ ማድረግ ነው። ለዚሁም ተገቢ የሆነው ቻርት ውስጥ ካርድ ወይንም ጠጠር በማስገባት እንዲያሳይ ማድረግ ነው። <u>ለምሳሌ</u> በአካባቢው ሕዝብ ላይ በተደጋጋሚ የሚታየውን በሽታ የሚያሳየው ቻርት የትኛው ነው?


- የምርጫው ውጤትም አብሮ ከሕዝቡ ጋር ይታያል ውይይትም ይደረግበታል።

ይህንን ዘዴ ለተለያዩ መረጃ ማጠናቀሪያነት ልንገለገልበት እንችላለን።

<u>ለምሳሌ</u>፣

- የእጅ መታጠብ (መቼ፣ በምን፣ እንዴት.....)፣
- ንጽሕ ምድር የት ይወጣሉ (ጎዜ፣ በጋራ ወይስ ለብቻ....) የሚገለገሉባቸውን ወይም የሚፈልጓቸውን በመለየት፣
- በመፀዳጃ ቤት የማይጠቀሙ የቤተሰብ አባላት ሁኔታ (ለምን)፣
- የውኃ ማጠራቀሚያ ሁኔታ፣
- የውኃ አቀዳድ ሁኔታ፣
- የውኃ አጠቃቀም፣
- የምግብ ንፅህና አጠባበቅ (ከዝግጅት እስከ አቀማመጥ)፣
- የምግብ ዕቃዎች ንፅህና አጠባበቅ (የት ይታጠባሉ የት ይቀመጣሉ)፣

በዚህ ዘዴ ኅብረተሰቡ እንደሚስጥር አድርጎ የሚቆጥራቸውን ጉዳዮች በቀላሉ ለማወቅ ቢያስችግርም በቅድሚያ ኅብረተሰቡ እንዲያውቀው የሚያስፈልገው እያንዳንዱ ሰው በሰጠው ምርጫ የግል አኗኗርን ለመገምገምና ለመውቀስ እንዳልሆነ ነገር ግን በአጠቃላይ የኅብረተሰቡን የአኗኗር ዘይቤ ለማወቅና ለመገምገም መሆኑን ማስረዳትና ማሳመን ያስፈልጋል።



## 2ሙ. የአካባቢያቸውን አቀማመጥ በጋራ መሣል

ይህ ካርታ የሚሰራው በኅብረተሰቡ ቢጋራ ሲሆን በሰፊ ወረቀት ወይም በመሬት ላይ በአንጨት በመጫር ሊሰራ ይችላል። ካርታው ላይ የሚሰፍሩት ነገሮች አብዛኛው ኅብረተሰቡ የሚያውቃቸው መሆን አለባቸው ለምሳሌ መንገዶች፣ ወንዞች፣ የቤቶች አቀማመጥ፣ ትምህርት ቤት፣ ጤና ጣቢያ፣ ቤተ ክርስቲያን፣ መስጊድ የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ።

ከነዚህም በተጨማሪ ሕዝቡ ለመፀዳጃነት የሚጠቀምበት የሕዝብ መፀዳጃ ቤት ወይም ሜዳ፣ ውኃ የሚቀዳበት አካባቢን፣ የቆሻሻ ችግር የሚታይበትን አካባቢ፣ የመሳሰሉትን አካባቢዎች በካርታው ላይ እንዲያመለክት ማድረግ።

አዲስ የውኃ ማደያም ሆነ የሕዝብ ሽንት ቤቶች የት አካባቢ ቢሠሩ የተሻለ እንደሚሆን ተስማምተው እንዲያመለክቱ ማድረግ፣ ቦታዎችን ለማመልከት ድንጋይ ወይም እንጨት በማስቀመጥ ሊያመለክቱ ይችላሉ።

ይህንን ካርታ ከወረቀት ይልቅ መሬት ላይ መሥራት የተሻለ ነው። በወረቀት ላይ ለመስራት ያልተማሩ ሰዎች በአብዛኛው አይደፍሩም። ብዙ ሰውንም ቢሆን ለማሳተፍ አመቺ አይሆንም። መሬት ላይ ከሆነ ግን ሰዎች ፍርሀት ስለማይኖርባቸው በሰፊው ሊሳተፉ ይችላሉ። ስህተት እንኳን ቢሠሩ ስህተቱን በቀላሉ ያለ ችግር ማስተካከል ይቻላል። መሬት ላይ የተሠራው ካርታ ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ ወረቀት ቅጂ ማድረግ ይቻላል በትክክል ቅጂ መደረጉንም ሕዝቡ እራሱ እንዲያረጋግጥ ማድረግ።

ይህ የካርታ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የሚከተሉትን ማድረግ፣

- የካርታው ሥራ አካባቢውን ለማወቅና እንዲሁም በየጊዜው የሚደረጉትን ለውጦች በቀላሉ ለመለየት የሚያስችል መሆኑን ለኅብረተሰቡ ማስረዳት፣

- የካርታው ሥራ በመጀመሪያ መሬት ላይ ቀጥሎም ወደ ወረቀት ቅጂ የሚደረግ መሆኑን በማስረዳት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችን በቅድሚያ ማዘጋጀት (በአካባቢው የሚገኙ ቅጠላ ቅጠሎች፣ አበባዎች፣ ፍሬዎች ወዘተ... ለመጠቀም መሞከር)፣

- በቅድሚያ ኅብረተሰቡ በአካቢቢው የሚገኙትን ዋና ዋና መንገዶችና እንዲሁም ወንዝ ድልድይ የመሳሰሉትን እንዲስል ማድረግ። በመቀጠልም ምን ምን ቦታዎች በካርታው ቢካተቱ እንደሚሻል በማወያየት ሥራውን መቀጠል። ካርታው በሚሰራበት ጊዜ ወንዶችም ሴቶችም እንዲሳተፉ ማድረግ።

በአጠቃላይ የካርታው ሥራ አንድ ሰዓት ያህል ሊፈጅ ይችላል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ከኅብረተሰቡ ውስጥ በሚገባ አካባቢያቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁትን፣ ችግር ያለበት አካባቢን እንዲሁም በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን አንዳንድ ቅራኔዎች ለማወቅ ይጠቅማል።



## 2ሠ. ገላጭ ስዕሎች (ፖስተሮች)

በሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ አሳዛኝ የሆኑና ሌሎች ሁኔታዎችን በስዕል በማስቀመጥ ኅብረተሰቡ እንዲያያቸው በማድረግ (ለምሳሌ የአካባቢ ስብሰባ፣ የታመመ ሰው፣ ውኃ ሲቀዳ፣ ወዘተ...) ታሪክ እንዲፈጥርላቸው ማድረግ። በዚህ ዘዴ ኅብረተሰቡ ውስጥ የሚገኙትን ዋና ዋና ችግሮችና ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችን እንዲሁም የኅብረተሰቡን እምነትና አስተሳሰብ በደበልጥ ለማወቅ ይቻላል። (ለምሳሌ የሚሆኑ ስዕሎች በሚቀጥሉት ገጾች ተያይዘዋል)።

- በቅድሚያ ተሳታፊዎቹን እስከ ስድስት ሰው በሚይዙ ትንንሽ ቡድኖች መከፋፈልና የተለያዩ ስዕሎችን የያዙ ፖስተሮችን መስጠት፣


- ከነዚህ ፖስተሮች ውስጥ ታሪክ ሊፈጥሩላቸው የሚችሉትን መርጠው እንዲያስቀሩ በማድረግ ታሪክ እንዲፈጥሩባቸው ማድረግ። ታሪኩም ቢቻል አንድ መነሻ ቢኖረው ይመረጣል። ለዝግጅቱም ከ20 እስከ 30 ደቂቃ መስጠት፣

- ታሪኩን አዘጋጅተው እንደጨረሱ ታሪኩን ከስዕሎቹ ጋር እያቀናጁ እንዲናገሩ ማድረግ፣

- የተዘጋጀው ታሪክም በአስተባባሪው ወይም ከኅብረተሰቡ መጻፍ በሚችል አባል በኩል በጽሁፍ እንዲያዝ ማድረግ፣

- በመጨረሻም በየቡድኖቹ ስለተፈጠሩት ታሪኮች ዝምድናና ልዩነት ኅብረተሰቡ እንዲወያይበት ማድረግ። በአካባቢው ቀዳሚ ትኩረት ሊሰጣቸው ስለሚገባቸው ጉዳዮች በመቀጠል መነጋገር ይቻላል። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን ስዕሎች ይመልከቱ፣














## 2ረ. የኅብረተሰቡን የኢኮኖሚ አቋም መለየት

ይህ ዘዴ የሚጠቅመው የኅብረተሰቡን አጠቃላይ የኢኮኖሚ አቅም ለማወቅ ነው። በኅብረተሰቡ መካከል የሚኖሩትንም አቅመ ደካሞችን ለይቶ ለማወቅ ይረዳል ነገር ግን ይህን ዘዴ በምንጠቀምበት ጊዜ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል። በተለይ ግለሰቦች ስለግለሰቦች የሚሰጡት አስተያየት ኅብረተሰቡ ውስጥ ቅራኔ ፈጥሮ አጠቃላይ የሥራችንን እንቅስቃሴ ወደ ችግር ሊመራው ይችላል።

የኅብረተሰቡን የኢኮኖሚ ሁኔታ ለማወቅ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ይቻላል። በአካባቢው ከሚሠሩ ልዩ ልዩ ድርጅቶች ጋር በመወያየት የአገር ሽማግሌዎችንና ግለሰቦችን በማነጋገር ወዘተ...። ከእነዚህም በተጨማሪ አካባቢውን በየሠፈሩ በመከፋፈል ስለ ሠፈሩ ጥልቅ ግንዛቤ ያላቸውን ግለሰቦች በመቅረብ ስለየሠፈሩ መረዳት ይቻላል።


ስለ አንድ አካባቢ ነዋሪ የኢኮኖሚ አቅም ለማወቅ በመጀመሪያ ሀብታም፣ መካከለኛ፣ ደሀ ብሎ ለመለየት ምን ላይ በመመርኮዝ እንደሆነ ስምምነት ላይ መድረስ ያስፈልጋል። ከዚህም በመቀጠል የአካባቢውን ሁኔታ በጥልቀት የሚያውቁትን ሰዎች ከየሠፈሩ በመምረጥ የሠፈራቸውን ነዋሪ እያንዳንዱን በየትኛው ደረጃ እንደሚመድቡት መረጃ ማግኘት ይቻላል። ለዚህ ሥራ ካርዶችንና የኪስ ወረቀቶችን መጠቀም ይቻላል። ከሠፈሩ በአባወራዎች ቁጥርና ስም ካርዶች በማዘጋጀና እነዚህን ካርዶች በኢኮኖሚ አቅም በተከፋፈሉት የኪስ ወረቀቶች ውስጥ በማስገባት የሠፈሩን ሕዝብ የኢኮኖሚ ሁኔታ ለመረዳት ይቻላል። በተለያዩ ሠፈሮች እንደዚሁ እየተሠራ የአጠቃላይ የአካባቢውን ገፅታ መረዳት ይቻላል።

ይህ ዘዴ የሚጠቅመውም በአካባቢው ለሚሠራው ማንኛውም ዓይነት ፕሮጀክት ቀዳሚ ተጠቃሚ ማን እንደሆነ፣ ሌላውንስ ተጠቃሚ ለማድረግ ምን ማድረግ እንደሚቻልና ከዚህም በተጨማሪ ይህ ጥናት በሚጠናበት ወቅት በአካባቢው ያሉት ችግሮች ከአካባቢው የኢኮኖሚ አቅም ጋር በማዛመድ ጠቃሚ መረጃዎችን ለማግኘት ይረዳል።


## 3. የመረጃ አጠቃቀም

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ዘዴዎች በቂ መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ የንጽሕና አጠባበቅ ትምህርት እንዴት መስጠት እንደሚገባው ዕቅድ ማውጣት፣ ዕቅዱም ከኅብረተሰቡ ጋር በመተባበር ይከናወናል።

በመጀመሪያ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በማነፃፀር ቻርቶችንና ምስሎችን በማዘጋጀት ለአካባቢው ሕዝብ በስብሰባ ማሳወቅ ይህን ለማድረግ ከዚህ በታች አንዳንድ ምሳሌዎች ቀርበዋል።




ስለ ኦ.አር.ኤስ ዝግጅት የሚያውቁ
በዐደማና በቂጦ-ዞን t 1995



ከዚህ ምሣሌ እንደምንረዳው ስለ ኦ. አር. ኤስ. ዱቄቱ ውስጥ የተወሰኑ ሰዎች ቢያውቁም ልጃገረዶች ግን በአብዛኛው እንደማያውቁ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ደግሞ ቤት ውስጥ የሚውሉና ሕፃናትን የሚጠብቁ ልጃገረዶች ናቸው። ስለዚህ ስለ ኦ. አር. ኤስ. በምናቅደው ትምህርት ዋነኛ ተሳታፊ መሆን ያለባቸው ልጃገረዶች መሆን እንዳለባቸው ማወቅ እንችላለን።

የንፅሕና አጠባበቅ ትምህርቱን ባቀድነው መሠረት ካካሄድን በኋላ በአካባቢው ኅብረተሰብ ዘንድ የአስተሳሰብና የተግባር መሻሻልና ለውጥ መኖሩን መከታተል ያስፈልጋል። በአካባቢው ብዙም መሻሻልና ለውጥ ካልታየ ትምህርቱን መመርመርና አንዳንድ ለውጦችን በማድረግ ትምህርቱን እራሱን ማሻሻል ያስፈልጋል። ይህንንም በምናደርግበት ጊዜ ከኅብረተሰቡ ጋር መሆን አለበት። ምክንያቱም ከትምህርቱ በኋላ ለምን መሻሻል እንዳልታየ ሊረዱ ይችላሉና።

በየትኛው የአካባቢ ንፅሕና ትምህርት ላይ መሳተፍ ይፈልጉ ዘንድ ውሳኔው መተው ያለበት ለራሱ ለኅብረተሰቡ ነው። የትምህርቱ ፕሮግራም እንደ መደበኛ ትምህርት አስተማሪ ለተማሪዎቹ ገለፃ በሚያደርግበት አኳኋን የሚካሄድ ሳይሆን እራሱ ኅብረተሰቡ በውይይት የሚሳተፍበት ዓይነት መሆን ይገባዋል። ስለዚህ ለውይይትም እንዲያመች የተሳታፊው ቁጥር ከ20 ባይበልጥ ይመረጣል።

ከዚህ በታች የሚገኙት ምሳሌዎች በ11 ከተሞች የመጠጥ ውኃና ሳኒቴሽን ጥናት ላይ የተገኙትን አንዳንድ መረጃዎች በተለያዩ ዘዴዎች እንዴት ማስቀመጥ እንደሚቻል ለማሳየት የሚረዱ ናቸው ።

## የ11 ከተሞች የንፅህና አጠባበቅ ሁኔታ በአማካይ

| ተራ ቁ. | የውኃና የንፅህና አጠባበቅ አርዕስት | ጠቅላላ ነጥብ (ከመቶ) |
|---|---|---|
| 1 | ንፁህ የመጠጥ ውኃ የሚጠቀሙ | 72 |
| 2 | ሁልጊዜ ንፁህ የመጠጥ ውኃ የሚያገኙ | 14 |
| 3 | የውኃ መቅጃው ክዳን ያለው | 100 |
| 4 | ከውኃ ማጠራቀሚያ የሚጠለቅበትን ዕቃ መሬት የማያስቀምጡ | 100 |
| 5 | ከሽንት ቤት መልስ እጃቸውን በሳሙና የሚታጠቡ | 46 |
| 6 | የሕፃናትን ዓይነምድር ከፀዱ በኋላ እጃቸውን የሚታጠቡ | 46 |
| 7 | ምግቦችን በጥንቃቄ ከድነው የሚያኖሩ | 100 |
| 8 | ያልታጠበ ፍራፍሬና አትክልት የማይበሉ | 86 |
| 9 | የምግብ ዕቃዎችን በጥንቃቄ የሚያስቀምጡ (በመደርደሪያ ወይም ጠረጴዛ ወዘተ...) | 70 |
| 10 | ቆሻሻን የሚያቃጥሉ ወይም በጉድጓድ የሚቀብሩ | 16 |
| 11 | የተጠቀሙበትን ውኃ ወደ ጉድጓድ ወይም ወደ ጓሮ በቦይ የሚያፈሱ | 18 |
| 12 | ከብቶችን ከመኖሪያ ቤታቸው ውጭ የሚያሳድሩ | 94 |
| 13 | በመኖሪያ ቤታቸው ዝንብ በብዛት የማይገኝ | 51 |
| 14 | የግል መፀዳጃ (ሽንት) ቤት ያላቸው | 64 |
| 15 | በመፀዳጃ ቤቱ ሁሉም የቤተሰቡ አባላት የሚጠቀሙበት | 59 |
| 16 | የሕፃናትን ዓይነምድር ወደ መፀዳጃ ቤት የሚጨምሩ | 34 |
| | ጠቅላላ ድምር | 958 |

## የንፅህና አጠባበቅ ሁኔታና ያጋጠሙ ችግሮች

| የፍላጎት መጠን | አጠቃቀም | ያጋጠሙ ችግሮች |
|---|---|---|
| ከፍተኛ | ንፁህ የመጠጥ ውኃ በየጊዜው ይጠቀማሉ | ነገር ግን ውኃውን በበቂ ሁኔታ አያገኙም ውኃውን ለመቅዳት አመቺ የሆነ ቦታ የላቸውም። |
| ከፍተኛ | ደረቅ ቆሻሻ የሚያቃጥሉ ወይም በጉድጓድ የሚቀብሩ | ኅብረተሰቡ ደረቅ ቆሻሻ የሚጥልበት ጉድጓድ በበቂ ሁኔታ አልተዘጋጀም። የተዘጋጀትም ተገቢው ክትትል አይደረግላቸውም። ሕዝቡ ደረቅ ቆሻሻን የትና እንዴት በጥንቃቄ መጣል እንደሚገባው በተደጋጋሚ ማስተማር ያስፈልጋል። |
| ከፍተኛ | የተጠቀሙበትን ውኃ (ፍሳሽ) በበይ ወደ ጉድጓድ ወይም ጓሮ ያስወግዳሉ | በከተሞች ውስጥ የሚገኙት የፍሳሽ ማስወገጃ ቦዮች በቂ አይደሉም። የተሠሩትም ቢሆን ተገቢው ክትትል አይደረግላቸውም። ሕዝቡ የትና እንዴት መጠቀም እንዳለበትና ተገቢ የሆኑ ዘዴዎችን እንዲያውቅ ማድረግ ያስፈልጋል። |
| መካከለኛ-ከፍተኛ | ከተፀዳዱ በኋላ እጅ ይታጠባሉ | በመፀዳጃ ቤት አካባቢ ውኃና ሣሙና (አመድ) በቀላሉ እንዲገኙ (በሴቶች የሚከናወን) በማድረግ የኅብረተሰቡን አመለካከት እንዲሻሻል በማድረግ ይህን ልምድ ማዳበር ይቻላል |
| መካከለኛ-ከፍተኛ | የሕፃናትን ዓይነምድር ካፀዱ በኋላ እጃቸውን የሚታጠቡ | በመፀዳጃ ቤት አካባቢ ውኃና ሣሙና (አመድ) በቀላሉ እንዲገኝ በማድረግና የኅብረተሰቡ አመለካከት እንዲሻሻል በማድረግ ይህን ልምድ ማዳበር ይቻላል |
| መካከለኛ-ከፍተኛ | የዘንብ ቁጥጥር | የአካባቢው የአየር ፀባይ ተፅዕኖ ቢኖረውም በአብዛኛው ግን የቆሻሻና የፍሳሽ አወጋገድ እንዲሁም የመፀዳጃ ቤት አጠቃቀም ልማድ ተፅዕኖ ያደርጋሉ። ምግብንና ውኃን የመከደን ልማድ መዳበር ይኖርበታል |
| መካከለኛ-አነስተኛ | ንፁሕ የመጠጥ ውኃ ያገኛሉ | የንፁህ መጠጥ ውኃ ሥርጭቱን ማሻሻል ውኃው የሚታደልበትን ጊዜና ቦታ ማሻሻል ዋጋውንም ከአካባቢው ሕዝብ ጋር ማጣጣም |
| መካከለኛ-አነስተኛ | መመገቢያ ዕቃዎችና የውኃ ክዳን በተገቢ ቦታ ይቀመጣሉ | የዕቃ መደርደሪያዎችና ማስቀመጫዎችን በማዘጋጀት የቤት ውስጥ ንፅህናን ማሻሻል ይቻላል። ስለዚህ እነዚህን ነገሮች ለመሥራት የሚቻልበትን መንገድ መቀየስ ያስፈልጋል |
| መካከለኛ-አነስተኛ | ሽንት ቤት ይጠቀማሉ | የሕዝብ ሽንት ቤቶችን ማስፋፋት ለግልና ለአካባቢ የሚሠሩ ሽንት ቤቶች አነስተኛን ወጪ የሚጠይቁ ሆነው እንዲሠሩ ቢደረግ ከተቻለም በብድር እንዲሠሩ ማድረግ |
| መካከለኛ-አነስተኛ | ሁሉም የቤተሰቡ አባላት በመፀዳጃ ቤት ይጠቀማሉ | በሚገኘው መፀዳጃ ቤት ሁሉም የቤተሰብ አባላት እንዲጠቀሙ ማድረግ |

በዚህ መመሪያ ውስጥ ኅብረተሰቡን ለማስተማር የሚያስችሉ አንዳንድ ዘዴዎች ቀርበዋል። ነገር ግን የትኛው ዘዴ በየትኛው ቦታ የሚለው ውሳኔ በአብዛኛው የሚሰጠው በአስተባባሪው እንዲሁም በሚሰበሰቡት መረጃዎችና ባለን የማስተማሪያ ቁሳቁሶችና በአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ይሆናል። እነዚህ ዘዴዎች ለተፈለገው አካባቢ እንዲያመቹ ተደርገው ተሻሽለውም ሆነ ተለውጠው ሊሠራባቸው ይችላል። በስዕሎቹ ላይ የሚታዩት የሰዎች አለባበስና የመሳሰሉት ትምህርቱ ከሚሰጥበት አካባቢ ባህል ጋር የተመሳሰለ መሆኑን በቅድሚያ ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

## 4. <u>የመማሪያ ዘዴዎች</u>

በዚህ መመሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተዘረዘሩት ዘዴዎች በአብዛኛው በኅብረተሰቡ ተሳትፎ የሚከናወኑ ሲሆን ነገር ግን ለሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ትምህርቱን የማስተላለፊያ መንገዱ ተመሳሳይ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ የእያንዳንዱ የኅብረተሰብ ክፍል አስተሳሰብና ሥነልቦና እንዲሁም የጎልማሶች የትምህርት አሰጣጥ ጥበብን በቅድሚያ ማወቅ ጠቀሜታ አለው ከእነዚህም አንዳንዶቹ፣

- ሰዎች በሚያረጁበት ጊዜ አንድ ነገር ቶሎ ማስታወስ ቢከብዳቸውም ነገሮችን ለመገንዘብ በጥልቀት ለመመርመርና ለመረዳት ያላቸው ችሎታ ይጨምራል፣

- ጎልማሶች ተማሪም አስተማሪም ስለሆኑ የጋራ ውይይት ማድረጉ ለትምህርቱ እጅግ ጠቃሚ ነው።

- ጎልማሶች በውድድር ላይ ከተመሠረተ የትምህርት ዘዴ ይልቅ በጋራ በመተባበርና በመደጋገፍ በሚፈጠር መማማሪያ መድረክ ብዙ ይማራሉ። ሁሉም የየራሳቸው ዕውቀትና ችሎታ እንዳላቸው መዘንጋት የለብንም፣

- ጎልማሶች ሰፋ ያለ ዕውቀት፣ ልምድ፣ የፈጠራ ችሎታና አመለካከት ስላላቸው ሊከበሩ ይገባል። በትምህርቱ ላይ ሁሉንም በማክበር ለማሳተፍ ጥረት ማድረግ፣

- ጎልማሶች በተግባር ብዙ የተማሩ ስለሆነ ትምህርቶች እነሱ ቀደም ብለው የሚያውቁትን መሠረት በማድረግ መነደፍ አለባቸው።

ከዚህ የሚከተሉት ተግባራት ተገቢ የሆነውን የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ሊጠቀሙ ይችላሉ።

## 4ሀ. የማሰላሰል ዘዴ

በዚህ ዘዴ ተሳታፊዎቹ የተሻለው የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ እንደ ተማሪና አስተማሪ ወይም በጋራ አብሮ የመማር ዓይነት መሆኑን በመለየት ተገቢ የሆነውን የመማሪያ ዘዴ ሊጠቁሙ ይችላሉ።

- ተሳታፊዎችን በተለያዩ አነስተኛ ቡድኖች በመከፋፈል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ገላጭ ስዕሎች መስጠት፣


- እያንዳንዱን ቡድን ከስዕሎቹ ውስጥ ተገቢ የመማሪያ ዘዴ ነው ብለው የሚያምኑበትን ሦስት ስዕሎች እንዲመርጡ ማድረግ፣ እንዲሁም ሦስት ለመማሪያ አመቺ አይደሉም የሚሏቸውን ስዕሎች እንዲመርጡ ማድረግ፣

- እያንዳንዱን ቡድን የመረጡበትን ምክንያት በየቡድኑ ከ10 እስከ 15 ደቂቃ እንዲወያዩበት ማድረግ። በመቀጠልም እያንዳንዱ ቡድን የመረጧቸውን ስዕሎች በግድግዳ ላይ እንዲሰቅሉ ማድረግ። ተገቢ ዘዴ ተብለው የተመረጡት አንድ ላይ እንዲሁም አያመቹም ተብለው የተመረጡት አንድ ላይ ይሆናሉ፣

- በመቀጠልም እያንዳንዱን ቡድን የመረጡበትን ምክንያት በመጠየቅ ለተሳታፊው እንዲያብራሩና እንዲወያዩበት ማድረግ። ለምሳሌ የሚሆኑ ስዕሎች በሚቀጥሉት ገጾች ይገኛሉ።


















COVER

## 4ለ. የጎልማሳ-ጎልማሳ እና የልጅ-የጎልማሳ መማማር

በዚህ ዘዴ በተማሪ አስተማሪ ጓደኝነት የማስተማሪያ ዘዴና በጋራ አብሮ በመማማር ዘዴ መካከል ያለውን ልዩነት በማወቅ ጎልማሶችን ለማስተማር ተገቢ የሆኑ መንገዶችን ይጠቁማል፣

- ከተሳታፊዎቹ መካከል በፍላጎት "አንድ እናት ልጇ ውኃ ለመቅዳት ብዙ ጊዜ በማጥፋቷ ስትቆጣ" የሚያሳይ አጭር ድራማ የሚሰሩ ሁለት ሰዎችን መምረጥ፣
- የተመረጡት ሰዎች አጭር ልምምድ ሲያደርጉ ተሣታፊዎችን የእናትየውን ሁኔታና የልጂቱን መልስ እንዲገምቱ ማድረግ፣
- ድራማው እንዲታይ በማድረግ ተሣታፊዎችን ስለ አጠቃላይ ሁኔታውና ስለ እናትየውና ስለልጅቷ ድርጊት ሀሳብ እንዲሰጡ ማድረግ፣
- በተራም ተሣታፊዎችን ሌላ አንድ ሰው እነሱን ልክ እንደ ልጅቷ ቢቆጣ ምን እንደሚያደርጉ መጠየቅ። በእውነተኛ ሕይወታቸውም የሚያስታውሱት እንደዚህ ያለ ሁኔታ ገጥሟቸው እንደነበርና እንዴት እንደተወጡት በመጠየቅ በፍላጎታቸው እንዲናገሩ ማድረግ፣
- በመጨረሻም ከተሣታፊዎች ከመሀላቸውም ሆነ ሌላ አንድ ታላቅ ሰው ስህተት ቢሠራ ስህተቱን እንዴት መንገር እንደሚገባን አስተያየቱ እንዲሰጡ ማድረግ።

## 5. የአካባቢ ንፅህና ትምህርት ተግባራት (ለትናንሽ ቡድኖች)

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የአካባቢ ንፅህና ትምህርት ተግባራት በተለያዩ አገሮች የተሞከሩ ሲሆን ውጤታማም እንደነበሩ ተረጋግጧል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችና ስዕሎች ተካተዋል። አንዳንዶቹም በኢትዮጵያ ውስጥ ያልተሞከሩ ናቸው። ስለዚህ እነዚህን ዘዴዎች በቀጥታ ተግባር ላይ ከማዋል በፊት ተስማሚ መሆናቸውንና አለመሆናቸውን መፈተሽ ያስፈልጋል። ያለበለዚያ በኅብረተሰቡና በእኛ መካከል አለመግባባት ሊፈጠር ይችላል። በቅድሚያ ትምህርቱ ሊሰጥ የታሰበበትን አካባቢ ባህልና አኗኗር ከሚያውቁ ሰዎች ጋር መፈተሽ ይገባል። እነዚህ ሰዎች ዘዴዎቹን ለመረዳት ካቃታቸው ከአካባቢው ሁኔታ ጋር ሊዋሀዱ በሚችሉበት መንገድ ለማጣጣም ሙከራ ማድረግ ያስፈልጋል።

## 5ሀ. የመተላለፊያ መንገዶች

የዚህ ክፍለ ጊዜ ዋና ዓላማ ለተሳታፊዎቹ ስለ በሽታዎች መተላለፊያ መንገዶችና መከላከያ ዘዴዎች ሀሳብ ለማስጨበጥ ነው። በዚህ ክፍለ ትምህርት መጨረሻ ላይ ተሳታፊዎች ስለተለመዱት ከውኃና ዓይነ ምድር ጋር ግንኙነት ስላላቸው በሽታዎች የመተላለፊያ መንገዶችና የት ላይ ይህንን የመታላለፊያ መንገድ መግታት እንደሚችሉ መግለጽ ይኖርባቸዋል።

- ተሳታፊዎችን 5 ወይም 6 ሰዎች ባካተተ ቡድን በመከፋፈል ለእያንዳንዱ ቡድን ቅደም ተከተሉን ባልጠበቀ ሁኔታ የበሽታ መተላለፊያ ሁኔታዎችን የሚገልፁ ሥዕሎችን መስጠት። (ለምሳሌ የሚሆኑ ሥዕሎች በሚቀጥሉት ገፆች ይገኛሉ)

- እያንዳንዱ ቡድን የሥዕሎቹን ቅደም ተከተል በመፈለግና በማስተካከል እንዴት በሽታዎች ሊተላለፉ እንደሚችሉ እንዲያሳዩ መምራት።


- ቡድኖቹ ስለመረጡት ቅደም ተከተል የበሽታ መተላለፊያ ዓይነት እንዲያብራሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት።

- የየቡድኖቹ ውጤት አጠቃላይ ውይይት ከመቅረቡ በፊት እያንዳንዱ ቡድን አንድ ወጥ ውሳኔ ላይ እንዲደርስ ጊዜ መስጠት። ቡድኖቹ እነዚህን የበሽታ መተላለፊያ መንገዶች ስለሚከላከሉበት ዘዴዎች አንድ የግንዛቤ ሀሳብ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ።

- በመጨረሻም ተሳታፊዎቹ መጠየቅ ያለባቸው ጥያቄ ከላይ የተጠቀሱትን የመፍትሔ እርምጃዎች የመውሰድ ኃላፊነት ያለበት ማነው የሚል ይሆናል።


<u>ማሳሰቢያ</u>:- ይህ ትምህርት በምሳሌዎች የተደገፈና ስለበሽታዎች መዛመት በሚያብራራ ሌላ የትምህርት ክፍለ ጊዜ መደገፍ ይኖርበታል። "በዓይን ስለማይታዩ ጥቃቅን ሕዋሳት" ቀላል የሆነ ግንዛቤ መስጠት ምናልባት ሊያስፈልግ ይችላል። አጉሊ መነፅር ማግኘት የሚቻል ከሆነ ለተሳታፊዎቹ አጠቃቀሙን በማሳየት በቀላሉ ሕዋሳቶቹን ማየት እንዲችሉ ሊረዳቸው ይችላል። በእንስራ ውኃ፣ ምግብ፣ እጆችና ዝንብን ወይም ጥቃቅን ህዋሳትን (በቁራጭ ወረቀት እንደ ምሳሌ በመጠቀም) ስለበሽታ መተላለፊያ መንገዶች ተግባራዊ ገለፃ ማድረግ ይችላል።

በተጨማሪም በተንቀሳቃሽ ስዕል ላይ የዝንብ ምስል በገመድ በማሰር በምግብና በቆሻሻ (ዓይነ ምድር) ላይ በማንቀሳቀስ ሰፋ ያለ ትምህርታዊ ገለፃ ማካሄድ ይቻላል።


DIRT
FOOD









5ለ. <u>ድራማ በመጠቀም</u> (ሀ)

የዚህ ክፍለ ጊዜ ዋና ዓላማ ለተሳታፊዎቹ የበሽታ መተላለፊያ መንገዶችን መከላከያ ዘዴና፤ የአካባቢው ሕዝብ አዳዲስ የመከላከያ ዘዴዎችን ዕንስ ሀሳብ ላለመቀበል ያለበት ችግር ምን እንደሆነ ግንዛቤ ሊያስጨብጥ የሚችል ነው። በክፍለ ጊዜው መጨረሻ ተሳታፊዎቹ ዋና ዋናዎቹን የበሽታ መተላለፊያ መንገዶችንና ከመተላለፊያዎቹም መንገዶች መሀል በሽታውን የትላይ ማገድ እንደሚቻል ማስረዳት ይኖረባቸዋል። እንዲሁም የበሽታ መከላከያ ዘዴዎችን በጥቂት የኅብረተሰበ ክፍል ዘንድ በተጨባጭ ለምን ተፈፃሚ ለማድረግ እንደማይቻል ገለፃ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

- እያንዳንዱ ቡድን ቀደም ብሎ በተካሄዱ እንቅስቃሴዎች ላይ በመመርኮዝ የተለያዩ የበሽታ መተላለፊያ መንገዶችን በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡና የበሽታውንም መነሻ መንስዔዎች እንዲሁም በሽታው እንዳይከሰት መከላከያው ዘዴ ምን እንደሆነ መጠየቅ፣

- ድራማው ከ5 እስከ 10 ደቂቃ ባለ ጊዜ ማለቅ ይኖርበታል፣

- ቡድኑ በተጨማሪ የተጠቀሱት መከላከያ ዘዴዎች ለምን ተቀባይነት እንደማይኖራቸው መግለፅ መቻል አለበት። ለምሳሌ:-

ወንድ ልጅ፣ "ዛሬ አስተማሪያችን ሽንት ቤት በምንሄድበት ጊዜ ዝንቦች ዓይነ ምድር ላይ ወይም በጉድጓዱ አፍ ላይ እንደሌሉና ካሉም ምግባችን ላይ ማረፍ እንደሌለባቸው ማረጋገጥ እንዳለብን ነግረውናል"

እናት፣ "ይህንን እንዴት ማድረግ እንችላለን"?

ሴት ልጅ፣ "አስተማሪያችን እንደነገሩን ዝንቦች እንዳይኖሩ ሽንት ቤታችንን በንፅህና መያዝና ለቀዳዳውም ክዳን በማበጀት፣ ሕፃኑ ወንድማችን እንኳን ሜዳ ላይ ሲፀዳዳ ዓይነ ምድሩን አንስተን ሽንት ቤት በመክተት እጃችንን በሳሙናና በውኃ በመታጠብ ነው"።

እናት፣ "አስተማሪው እኔ እንዴት የሽንት ቤት ክዳን እንዳሠራ፣ የልጁንስ ዓይነ ምድር በየጊዜው እየጠረኩ ሽንት ቤት ለመክተት ጊዜውንስ ከየት አገኛለሁ? ደግሞስ ቶሎ ቶሎ እጃችንን በሳሙና ለመታጠብ ሳሙናውስ ከየት ይገኛል ብለው ያስባሉ?"

- እናም ድራማው ሊቀጥል ወይም መፍትሔ የማይገኝለትም ሆኖ ሊያልቅ ይችላል። ዋናው ቁም ነገር ግን ከአጠቃላይ ቡድኑ ጋር መከላከያ እንቅስቃሴዎቹን ወይም መንገዶቹን ተፈፃሚ ለማድረግ የሚገጥሙ አንዳንድ መሰናክሎችንና እነዚህንም መሰናክሎች በምን ዓይነት መንገድ መፍትሔ ሊፈለግላቸው እንደሚቻል ውይይት ማካሄድ ነው።

5ሐ. <u>ድራማ በመጠቀም</u> (ለ)

የዚህ ክፍለ ጊዜ ዋና ዓላማ የተሻለ የንፅህና ሁኔታዎች እንዳይፈጠሩ ለሚሸፍኑ ክስተቶች መፍትሔ ለመፈለግ ውይይት ማካሄድ ነው። በክፈለ ጊዜው መጨረሻ ተሳታፊዎች በአካባቢያቸው ነዋሪዎች ዘንድ ጎልቶ የሚታይና የተለመደ ችግር መግለፅና ለዚህም ችግር መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ ሀሳቦችን ማመንጨት ይኖርባቸዋል።

- ተሳታፊዎችን 5 ወይም 6 ሰዎች ባካተተ ቡድን መከፋፈል፣
- ለእያንዳንዱ ቡድን ከታች ከተዘረዘሩት ርዕሶች መሀል (ቡድኑ የራሱን ርዕስ ማቅረብ ይችላል) መስጠት፣
- በተሰጠው ርዕስ ላይ በመመረኮዝ እያንዳንዱ ቡድን በአካባቢው ኅብረተሰብ ላይ በተለየ ሁኔታ ተከስቶ በሚገኝ ችግር ላይ በማተኮር አጠር ያለ ድራማ እንዲያዘጋጅ ማድረግ (መጠየቅ)። ድራማው ከ5 እስከ 10 ደቂቃ ባለ ጊዜ ውስጥ ማለቅ ይኖርበታል።
- ቡድኑ ድራማው መፍትሔ ሳይጠቁም እንዲያልቅ ሆኖ ማዘጋጀት ይኖርበታል። በድራማው መጨረሻ ተመልካቹ (አዳማጩ) ኅብረተሰብ ውይይቶችን በማካሄድ ስለ ድራማው መልዕክት አንድ የመፍትሄ ሀሳብ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ፣

የክፍለ ጊዜው አቀናባሪ (መሪ) አንዳንድ ውኃና ንፅህና ያሉትን የግንኙነት ሀሳቦችን መሰንዘር ይኖርበታል።

**ለምርጫ የቀረቡ ርዕሶች፣**

- ከተማው የሚያስፈልገው ነገር፣
- አብዛኛዎቹ የቤት እመቤቶች ቀላል ስራ ይሰራሉ፣
- ተደጋጋሚ ሀዘን፣
- አሊ ለምን ታመመ?
- ከእንግዲህ ትምህርት ቤት የለም?

5ሙ. <u>ጤነኛ ሕፃን</u>

የዚህ እንቅስቃሴ ዋና ዓላማ ተሳታፊዎቹ በአካባቢያቸው ስላለ ጠንካራና ደካማ የንፅህና አጠባበቅ እንቅስቃሴዎች እንዲመረምሩ የሚያስችላቸው ይሆናል። በክፍለ ጊዜው መጨረሻ ተሳታፊዎቹ በአካባቢያቸው ሕፃናትን በጤናማ ሁኔታ ለመጠበቅ የተለመዱ ጠንካራ የንፅህና ማሻሻያ እንቅስቃሴዎችን መጠቀም (ማወቅ) ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም በአካባቢያቸው የተለመደ ደካማ የንፅህና አጠባበቅ ሁኔታዎች ምን ዓይነት ገፅታ እብዳላቸውና በምን ዓይነት ሁኔታ የበሽታ መንስኤ እንደሚሆኑ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይገባል።

- ሁለት ዓይነት የሕፃን ሥዕል (ጤነኛና የታመመ ሕፃን) ፊት ለፊት ባለግድግዳ ወይም ቦርድ ላይ መስቀል (መለጠፍ)፣ (በሚቀጥለው ገፅ ላይ ያለውን ሥዕል ይመልከቱ)


- ተሳታፊዎችን በሁለት ቡድን በመክፈል፣ ለሁለቱም ቡድን ሁለቱን ዓይነት የሕፃናት ስዕሎች መስጠት፣


- ለቡድኖቹ የትኛው ልምድ (እንቅስቃሴ) ለታመመው ልጅ ምክንያት እንደሆነና የትኛው ደግሞ የጤነኛው ልጅ መገለጫ ሊሆን እንደሚችል ጥያቄ ማቅረብ፣

- አንድ ወይም ሁለት ሰዎች ከቡድኑ በመምረጥ ቡድኑ የወሰነውን ሀሳብ እንዲገልፁና የትኛው ዓይነት እንቅስቃሴ ከየትኛው የሕፃን ሥዕል ጋር እንደሚገናኝ እንዲያሳዩ ማድረግ፣

- ተሳታፊዎቹን ከላይ የተዘረዘሩት እንቅስቃሴዎች ምን ያህል በአካባቢያቸው አዘውትረው እንደሚታዩ መጠየቅና ተጨማሪ ሀሳቦችም ስለሁኔታው በአካባቢያቸው ካሉ በዝርዝር እንዲያቀርቡ ማድረግ፣

<u>ማሳሰቢያ</u> አዘጋጁ በአካባቢው መሠረታዊ የንፅህና እንቅስቃሴ ጥናት ላይ የተመረኮዘ ለየት ያሉ ሁኔታዎች (እንቅስቃሴዎች) ካሉ ክፍለ ጊዜው ከማለቁ በፊት ሥዕላዊ መግለጫ ማቅረብ ይኖርበታል።





## 5ሠ. የተቅማጥ በሽታ ሕክምና

የዚህ ክፍለ ጊዜ ዋና ዓላማ የትምህርቱ ተሳታፊዎች ለተቅማጥ በሽታ በጣም ፍቱን ስለሆነ የህክምና ዘዴ ግንዛቤ ማስጨበጥ ነው። በዚህ ክፍለ ጊዜ መጨረሻ ላይ ተሳታፊዎቹ በ ኦ.አር.ኤስ መፈወስ የሚችሉትን በሽታዎች መግለፅና በትክክል በመመጠን ኦ.አር.ኤስ ማዘጋጀት መቻል ይጠበቅባቸዋል።

- በተቅማጥ በሽታ የታመመ ሕፃን ሥዕል ግድግዳ ላይ በማንጠልጠል ተሳታፊዎችን በሕፃኑ ላይ የተከሰተው በሽታ ምን ሊሆን እንደሚችል ሀሳብ እንዲሰጡ መጠየቅ። ምናልባት የአካባቢው ኅብረተሰብ የሚጠቀምባቸው የተለያዩ ባህላዊ ስሞች ይኖሩ ይሆናል፣

- በተደጋጋሚ አንድ ሕፃን በተቅማጥ በሽታ ቢጠቃ ምን ሊደርስበት እንደሚችል ተሳታፊዎቹ እንዲወያዩበት መጠየቅ፣

- ሁለተኛውንና በሰውነት ውስጥ ያለውን ፈሳሽ የጨረሰ ሕፃን ሥዕል በግድግዳ ላይ በመለጠፍ (በማንጠልጠል) ተሳታፊዎቹ ስለልጁ የህመም ገፅታ አስተያየት እንዲሰጡ መጠየቅ፣


- የደረቀ ወይም የጠወለገ አትክልት ለታሳታፊዎቹ በማሳየት ሌሎችም ህይወት ያላቸው ነገሮች በሙሉ በቂ ውኃ ሲያጡ ምን ዓይነት ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል ማስረዳትና የተሳታፊዎችንም አስተያየት መጋበዝ፣


- ብዙ ውኃ ከሰውነቱ የወጣው ሕፃን ልክ እንደ አትክልቱ በመጠውለግ ሊሞት እንደሚችል ማስረዳት፣

- በተቅማጥ ለታመመ ሰው ምን ዓይነት ሀክምና እንደሚደረግለትና የትኞቹ የሀክምና ዓይነቶች ውኃ ለታመመው ሰው ሊተኩ እንደሚችሉ መጠየቅ፣

በመጀመሪያዎቹ የተቅማጥ በሽታ ምልክቶች ታማሚው ሰው ተጨማሪ የሚጠጣ ነገር ወይም ፈሳሽ ምግብ እንዲሰጠው ግንዛቤ ማስጨበጥ። ነገር ግን ምንም ዓይነት የጤንነት መሻሻል ከሌለና ተቅማጡ ከቀጠለ ኦ.አር.ኤስ በመባል የሚታወቀውን ልዩ ፈሳሽ ማዘጋጀት።

ተግባራዊ የሆነ የኦ.አር.ኤስ አዘገጃጀት ትምህርት መስጠትና ተሳታፊዎችንም በቡድን በመከፋፈል እራሳቸው እንዲያዘጋጁ ማድረግ (የአዘገጃጀቱ ሥዕላዊ መግለጫ በሚቀጥለው ገፅ ላይ ይገኛል)።





## 5ረ. የኦ.አር.ኤስ አዘገጃጀትና አቀማመሙ (ጨዋታ)

የዚህ ክፍል ጊዜ ዋና ዓላማ ስለ ተቅማጥ በሽታ ህክምና ዕውቀትን በይበልጥ ለማዳበር ነው። በዚህ የትምህርት ክፍል መጨረሻ ተሳታፊዎቹ ኦ.አር.ኤስ ለማዘጋጀት ትክክለኛውን የጨው፣ የስኳርና የውኃ መጠን ማወቅና ሌሎች ሰዎችን ስለ ተቅማጥ በሽታ ህክምና መርዳት ይኖርባቸዋል።

- ምን ዓይነት የተቅማጥ በሽታ ህክምና ዘዴ እንደሚጠቀሙ ተሳታፊዎችን መጠየቅና ስለዚህ የተለያዩ ዘዴዎች ጥቅምና ጉዳት መወያየት፣


- ተሳታፊዎችን በትንንሽ ቡድኖች መከፋፈልና ለእያንዳንዱ ቡድን ኦ.አር.ኤስ ካርዶችን ማደል

- እያንዳንዱ ቡድን የተሰጠውን ካርዶች በመበወዝ ለያንዳንዱ ተሳታፊ ሦስት ሦስት ካርድ በማደል ቀሪዎቹን ካርዶች መገልበጥና እመሀል ጠረጴዛ ላይ ማስቀመጥ፣ (በሚቀጥሉት ገፆች ላይ ያሉትን ሥዕሎች በመቆራረጥ ካርዶችን ማዘጋጀት ይቻላል)


- እያንዳንዱ ተሳታፊ የተሰጠውን ካርዶች መመልከት ይኖርበታል። ከተሰጡት ካርዶች ውስጥ ትክክለኛውን የኦ.አር.ኤስ አዘገጃጀት የሚገልፁትን ካርዶች መርጦ በማውጣት ሌሎች ተሳታፊዎችን መቅደም ነው፣

- እያንዳንዱ ተሳታፊ በየተራ እመሀል ከተቀመጡት ካርዶች ውስጥ አንድ በማንሳት ጠቃሚ መሆኑንና አለመሆኑን ይወስናል። ያነሰው ካርድ ቀድሞ ከተሰጠው የተሻለ ጠቃሚ ነው ብሎ ካመነ ካርዱን መውሰድ፤ ነገር ግን በምትኩ ከቀደሞው ውስጥ አንድ ካርድ እመሀል ተደራርበው ከተቀመጡት ካርዶች ሥር ማስቀመጥ ይኖርበታል።


- በማንኛውም ጊዜ አንድ ተሳታፊ በቅደም ተከተል ትክክለኛውን የአዘገጃጀት ካርዶች ሲያሟላ "አሸናፊ" ብሎ መናገርና ካርዶቹንም በቡድኑ መሐል በማስቀመጥ ማሳየት ይኖርበታል። ሌሎች የቡድኑ አባላትም ካርዶቹ ትክክለኛ የአዘገጃጀት ቅደም ተከተል መያዛቸውን በማየት ማረጋገጥና አሸናፊነቱን ማፅደቅ ይኖርባቸዋል።


የኦ.አር.ኤስ. ፈሳሽ አዘገጃጀት
ስኳር
አንድ ሙሉ
ማንኪያ ስኳር
ጨው
ትንሽ ጨው
/በማንኪያ ጫፍ ለክ/
በብርጭቆ ውሃ
ሁል ጊዜ የተዘጋጀው
ኦ.አር.ኤስ. እንባ
እንባ የሚል የጨው
ጣዕም እንዲኖረው
ያስፈልጋል

የኦ.አር.ኤስ. አቀማመም ስለት ጠዋታ




ለሠስቱም ተጫዋቾች ለእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ካርዶች ያስፈልጋል




ካርዶቹን ከርክሞ በማውጣት መጫወት

## 5ሰ. ሦስት ቦታ ካርዶችን መለየት

የዚህ ልምምድ ዋና ዓላማ ተሳታፊዎቹ የአካባቢው ሕዝብ በአብዛኛው ጊዜ በሚያካሂደው የተለመደ እንቅስቃሴ ላይ የተመረኮዘ ውይይት እንዲያካሂዱ ድጋፍ መስጠትና ሁኔታውም በነሱ አስተሳሰብ ምን እንደሚመስል እንዲያጤኑት ማድረግ ነው።

በክፍል ጊዜውም መጨረሻ ተሳታፊዎቹ በአካባቢያቸው ኑዋሪዎች መካከል ስለሚከናወኑ ጠንካራና ደካማ እንቅስቃሴዎች ማወቅ ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም መሠራት ስላለባቸው ሁኔታዎች አላፊነቱን መውሰድ ያለበት ማን እንደሆነ መግለጽ (መጠቆም)፣ ለችግሮቹ መፍትሄ መፈለግና እንቅስቃሴዎቹም ላይ በተግባር መሳተፍ ይኖርባቸዋል።

በዚህ ጥራዝ ውስጥ የሚገኙ ሥዕሎችን እንዳመቺነታቸው በትናንሹ በመቆራረጥ ወይም የክፍል ጊዜው አቅራቢ ያዘጋጀው ሥዕሎች ካሉ በዚህ ልምምድ ወቅት መጠቀም ይቻላል።

- ተሳታፊዎችን ከ5 እስከ 6 ሰው ባካተተ ቡድን መከፋፈል፣

- ለእያንዳንዱ ቡድን የተለያዩ የካርድ ሥዕሎች ሰብስብ በመስጠት ሦስት ቦታዎች ላይ እንዲከፋፍሉ ማድረግ፣ ይኸውም ጠንካራ፣ ደካማና ጤናን በሚመለከት ረገድ ተመሳሳይ እንቅስቃሴዎችን የሚያካትት ይሆናል፣

- የክፍል ጊዜው ዓላማ ተሳታፊዎቹ በአካባቢያቸው ኅብረተሰብ ዘንድ የሚደረገውን እንቅስቃሴና ባህርያት መሠረት በማድረግ በተቻለ መጠን ሰፋ ያለ ውይይት እንዲያደርጉ መሆኑን መግለፅ፣

- ቡድኖቹ አንድ ወይም ሁለት በአካባቢያቸው ያሉ ችግሮችን የሚጠቁም ስዕላዊ ካርድ እንዲያነሱ ማድረግና ያንንም ችግር ለመቋቋም ምን ዓይነት እንቅስቃሴ መደረግ እንዳለበት እንዲገልፁ መጠየቅ ኃላፊነቱንም ከኅብረተሰቡ ውስጥ ማን መውሰድ እንዳለበት በዚህ አጋጣሚ ሊገልፁ ይችላሉ።

- ተሳታፊዎቹ ካርዱ ላይ ያሉትን ስዕሎች በተለያየ አቅጣጫ እንዲመለከቷቸው እገዛ ማድረግ፣ ለምሳሌ፦ ውኃን ማፍላትና መጠጣት ከጠንካራ እንቅስቃሴዎች አኳያ አንዱ ሆኖ ሊመረጥ ይችላል ግን ማገዶ በአካባቢው እንደልብ ባይገኝ ወይም ውድ ቢሆን ሁኔታው እንዴት ሊታይ ይችላል?

- በተጨባጭ በአካባቢው ስላሉ ችግሮች ምን ዓይነት የመፍትሔ እንቅስቃሴዎች መታሰብ እንዳለባቸው ተሳታፊዎችን መጠየቅ።

## 5ሸ. የችግር ሁኔታዎች

የዚህ ትምህርት ክፍል ዓላማ በተቀናጀ ዘዴ የተለመዱ የንፅህና ችግሮችና መፍትሔያቸውን መቃኘትና በአካባቢው የሚገኝ ቁሳቁስ (ሀብት) ለሂደቱ ምን ያህል ይጠቅም ወይም ይጎዳ እንደሆነ ጠቅለል ያለ ግንዛቤ ማሰባሰብ ነው። በዚህ ትምህርት ክፍል ጊዜ መጨረሻ ተሳታፊዎቹ በሽታ ሊያስከትሉ የሚችሉ የተለመዱ ችግሮችን መጥቀስ፣ ለችግሮቹ መፍትሔ መሻትና በአካባቢያቸው ለችግሮቹ ማስወገጃ ሊያገለግሉ የሚችሉ ሐብቶችን (ቁሳቁሶችን) መግለፅ ይኖርባቸዋል።

- ተሳታፊዎችን 5 ወይም 6 ሰዎች ባካተተ ቡድን መከፋፈል፣


- ለእያንዳንዱ ቡድን አንዳንድ ንፅህናው የተጎደለ ሁኔታ የሚያሳይ ሥዕል መስጠትና ሥዕሉ ላይ ያለው ችግር ምን እንደሆነ ለይተው እንዲገልፁ መጠየቅ። የሚገልፁት ችግር ትክክለኛውን ሁኔታ የተከተለ አባባል መሆን አለበት፣ ለምሳሌ፦ "የንፅህና ጉድለት" ከማለት "ሰዎች በውኃ ጉድጓድ አጠገብ ሲፀዳዱ" ወይም "ሰዎች እጃቸውን ከተፀዳዱ በኃላ ያለመታጠባቸው" ወዘተ... በማለት የጉድለቱን መንስዔዎች ዘርዘር ባለ ሁኔታ መግለፅ፣

- ተሳታፊዎቹ ለምሳሌ በሚቀጥለው ገፅ ላይ የሚታየው ሥዕላዊ መግለጫ የእነሱን አካባቢ ሁኔታ ያንፀባርቃል ብለው እንዲያስቡ ማድረግና በአካባቢያቸውም ሥዕሉ ላይ የሚታየውን የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን የሚያካሂዱት ከእኛው መሐል ያሉ ሰዎች ናቸው ብለው ቢገምቱ፤ ለእንቅስቃሴዎቹ የመፍትሄ ሐሳቦች ይሆናሉ ብለው የሚገምቱትን አስተያየት እንዲጠቁሙ መጠየቅ፣

- እያንዳንዱ ቡድን ስለችግሮቹና የመፍትሄ ሀሳቦች ያለውን ግንዛቤ ለአጠቃላይ ተሳታፊዎች ማቅረብ አለበት፣

- እያንዳንዱ ቡድን በሥዕሉ ላይ የሚታዩትን ድርጊቶች ኅብረተሰቡ መፍትሄ ሊፈልግላቸው ያልቻለበትን ምክንያት እንዲያሰላስሉ መጠየቅ፣

- የኅብረተሰቡን ችግር ለማስወገድ የሚያስችል በአካባቢው ምን ያህል ቁሳቁስ (የሀብት አቅም) ሊገኝ እንደሚችል ተሳታፊዎቹ እንዲወያዩበት ማድረግ።



## 5ቀ. <u>የሴቶች ሚና</u>

የዚህ ክፍለ ጊዜ ዋና ዓላማ ውኃንና ንፅሕናን በተመለከተ የሴቶችና የወንዶች ሚና ምን ዓይነት መልክ መያዝ እንዳለበትና በተጨማሪም ሴቶች በዕቅድ ማውጣትና ውሳኔ በመስጠት ላይ ሰፋ ባለ ሁኔታ እንዲሳተፉ በሚደረግበት ረገድ ላይ ውይይት እንዲካሄድ ማበረታታት ነው። በክፍለ ጊዜው መጨረሻ ተሳታፊዎቹ (ወንዶችና ሴቶች) በአንድ ላይ የሚሳተፉበት ሥራዎች (እንቅስቃሴዎች) ምን እንደሆኑ መዘርዘር ይኖርባቸዋል። እንዲሁም የዘረዘሯቸው ክንውኖች ምን ያህል ተቀራራቢነት እንዳላቸው፣ እያንዳንዱም ሥራ ምን ያህል እውቀትና ልምድ እንደሚያስፈልገውና እነዚህንም ሥራዎች ተፈፃሚ ለማድረግ ውሳኔውን መስጠት የማንኛው ክፍል ተሳትፎ እንደሆነ መግለፅ መቻል ይኖርባቸዋል።


- ተሳታፊዎችን በቡድን መከፋፈል፣ የወንድና የሴቱን ቁጥር በተቻለ መጠን እኩል ማድረግ (ወንዶች ትምህርቱ ላይ ከተሳተፉ)፣


- ለእያንዳንዱ ቡድን የተለያዩ ሥራዎችን ያካተቱ ካርዶች በመስጠት፣ ሦስት ቦታ ላይ እንዲለዩት ማድረግ። ይኸውም በሴቶች ብቻ፣ በወንዶች ብቻና በወንዶችም በሴቶችም በቅንጅት የሚከናወኑ ሥራዎችን ይሆናል። (በሚቀጥለው ገፅ ሥዕል መጠቀም ይቻላል)


- ይህ ሙከራ (ክፍለ ጊዜ) የተነደፈው የተለያዩ የወንድና የሴት ሥራዎች ላይ በማተኮር ገንቢ የሆነ አመለካከቶችን ለማዳበር ውይይት እንዲካሄድ እገዛ ለማድረግ ነው

- ሰፋ ያለ ውይይት እንዲካሄድ በማድረግ ለእያንዳንዱ የሥራ ዓይነት ምን ዓይነት ዕውቀት እንደሚያስፈልግና ሥራውን ተፈጻሚ ለማድረግ በቅድሚያ ምን ዓይነት ውሳኔ እንደሚያስፈልግ ተሳታፊዎቹን መጠየቅ፣


- በመጨረሻም ተሳታፊዎችን (ቡድኖቹን) ለእያንዳንዱ የተለያየ የሥራ ዓይነት ውሳኔ የመስጠቱ ኃላፊነት የማን ሊሆን እንደሚችል ያላቸውን ግምት መጠየቅ።













## 5በ. <u>በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተደገፈ ጥናት</u>

የዚህ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ዓላማ አንዳንድ ሊሳኩ ወይም ኅብረተሰቡን ሊያሳትፉ ያልቻሉ የንፅህና ትምህርት ዕቅዶችን ለመመልከት ነው። በዚህ ትምህርት መጨረሻ ተሳታፊዎቹ ለምን አንዳንድ የንፅህና ትምህርት ዕቅዶች ግባቸውን ሊመቱ እንዳልቻሉ መግለፅና ለተሻለ ውጤትም በምን ዓይነት ነጥቦች (ሁኔታዎች) ላይ የተመረኮዘ ዕቅድ መዘጋጀት እንዳለበት መወሰን ይኖርባቸዋል።

- የሚከተለውን በተጨባጭ ሁኔታ የተደገፈ ጥናት ለተሳታፊዎቹ በማንበብ አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግ፣

- ለምን ተስፋዬ ያቀረበው አዲስ ዕቅድ ተቀባይነት ለማግኘት በቂ ያልሆነበትን ምክንያት ተሳታፊዎቹ እንዲገልፁ መጠየቅ፣

- የጥናቱን ጽሑፍ እንደገና በማንበብ ለምን ኅብረተሰቡ የተስፋየን አዲስ የሀሳብ ዕቅድ ሊቀበል እንዳልቻለ የሚጠቁም ሀሳቦችን ከምንባቡ ውስጥ ለይተው ለማውጣት እንዲሞክሩ ማድረግ፣

- ተስፋየ ምን ዓይነት አበረታች ሁኔታዎች ቢጠቀም የአካባቢውን ሰዎች ለተሻለ ተሳትፎ ሊጋብዛቸው እንደሚችል የተሳታፊዎችን ሀሳብ መጠየቅ።

**የጥናቱ ዘገባ**

ተስፋየ የኅብረተሰብ ተሳትፎ አደራጅ ሲሆን በቅርቡ በአርባምንጭ በተካሄደው የንፅህና ትምህርት አውደ ጥናት ላይ ተሳታፊ ነበር። አውደ ጥናቱም የውኃ ብክለትን መከላከያ ዘዴዎች አዲስ እውቀት ያስጨበጠው ሲሆን ይህንን አዲስ ዕውቀት ሥራ ላይ ለማዋልና ለሌሎች ለማሳወቅ ሀይለኛ ጉጉት ነበረው።

ወዲያውኑ ወደ ምድብ ሥራው እንደተመለሰ ወሮታ ወደምትባል ትንሽ ከተማ ለመስክ ሥራ ወጣ። ከከተማዋ ባለሥልጣኖችና ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ ድርጅቶች ጋር ባደረገው ንግግር ጥቂት ሰዎች ብቻ የሽንት ቤት ተጠቃሚዎች እንደሆኑና ያሉትም ሽንት ቤቶች ባግባቡ ያልተገነቡና በንፅህናም እንዳልተያዙ ለመገንዘብ ቻለ። ልጆች (ሕፃናት) የትም ሜዳ ላይ እንደሚፀዳዱና ጥቂተ ሰዎች ብቻ ከመብላታቸው በፊት ወይም ከተፀዳዱ በኋላ እጃቸውን በሳሙና እንደሚታጠቡ በተጨባጭ መረጃዎች ሰበሰበ።

የከተማው የቧንቧ ውኃ ሥርጭት ዕሑድ ዕሑድ አይሠራም። ነዋሪዎቹም የቧንቧ ውኃ በማያገኙበት ወቅት ውኃ የሚቀዱት በአግባቡ ካልተጠበቁ ምንጮችና ጉድጓዶች ነበር። በነዚህ የውኃ መገኛዎች አካባቢ እንስሳት ሳር የሚግጡ ሲሆን እዳሪያቸውም ውኃውን የመበከል እድሉ ሰፋ ያለ ነበር። ተስፋዬ ለቀበሌው ሊቀመንበር የውኃ ኮሚቴ እንዲቋቋምና ነዋሪውን ሕዝብ በተጨማሪነት የሚያገለግሉትን የውኃ መገኛዎች ከብክለት እንዲከላከል ሁኔታዎችን እንዲያመቻች ሀሳብ አቀረበ።

ለተቋቋመው የውኃ ኮሚቴ አግባብ ስላለው የንፅህና አያያዝ ሁኔታ ላይ የተመረከዘ ሥልጠና በሱ በኩል እንዲሰጣቸውና በየኗሪው ቤትና በአንዳንድ ቦታዎች እየዞሩ መልዕክቱን እንዲያስተላልፉና እግረ መንገዳቸውንም አግባብ የሌለው የንፅህና ሁኔታዎች በየቤቱ ሲያጋጥማቸው የማሻሻያ ዘዴዎችን እያስተማሩ እንዲያልፉ ሀሳብ አቀረበ። እቅዱም ተቀባይነትን ስላገኘ ሁኔታዎችን አመቻችቶ ወደ መደበኛ ሥራው አመራ።

የኮሚቴው አባሎችም በተስፋዬ ትምህርትና ሀሳብ ላይ በመመርኮዝ ሥራቸውን ተያያዙት። በርካታ ቤቶችንና አንድ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት በጥንድ በጥንድ በመሆን ጎበኙ። በት/ቤቱም ውስጥ በሚገኝ አዲስ የተገነባ ሽንት ቤት አካባቢ የእጅ መታጠቢያ ውኃ ስላልነበረ ርዕሰ መምህሩን ስለ ሁኔታው አነጋገሩት። ርዕሰ መምህሩም ከሌሎች አስተማሪዎች ጋር እንደሚነጋገርበት በመግለፅ፤ በት/ቤቱ ውስጥ እያንዳንዱ ግለሰብ ይህንን አዲስ ሽንት ቤት ለማግኘት ምን ያህል እንደደከመ ኮሚቴው ግን በት/ቤቱ ውስጥ የኃላ ችግር እንዳለ አድርጎ ጥያቄ ማንሳቱ በጣም እንዳሳዘነው ነገራቸው።

የኮሚቴው አባላት ጉብኝታቸውን እንዳገባደዱ በርካታ የከተማው ነዋሪ ሕዝብ ለቀበሌው ሊቀመንበር ተቃውሞ ማቅረብ ጀመረ። ስለ ኮሚቴዎችም ጉብኝት ዓላማ ዝርዝር ገለፃ እንዲደረግለት ጠየቀ። ኮሚቴውም ሽንት ቤት የሌላቸውን ሰዎች መቃወምና እጃቸውንም መቼ ሳሙናና ውኃ በመጠቀም እንደሚታጠቡ መጠየቁ አግባብ አይደለም ሲሉ አወዙ።

በሌላ ጊዜ ተስፋዬ ያቀደውንና ያስጀመረውን እንቅስቃሴ ሁኔታ ለመመልከት ወደ ወሮታ ተመለሰ። ወዲያውም የኮሚቴውን አባላት ያካተተ ስብሰባ አዘጋጅቶ ውይይት ተጀመረ። ግን የኮሚቴው አባላት በመጀመሪያ ሲሰማሩ የነበራቸው ሞራል ሁሉ ወድቆ በማግኘቱ ተገረመ። የኮሚቴው አባላትም የሆነውን ሁሉ አስረዱት። የቀበሌውም ሊቀመንበር ስብሰባው ላይ ተካፍሎ ስለነበር ያለው አማራጭ የከተማውን ሰው ሁሉ ሰብሰባ አዘጋጅቶ በመጥራት ለተከሰተው ችግር በጋራ መፍትሄ ለመፈለግ ጥረት ቢደረግ ሁኔታዎች ሊመቻቹና የተስፋዬ ዓላማም ግቡን ሊመታ እንደሚችል ሀሳብ አቀረበ።

5ተ. <u>ታሪኮችን መጠቀም</u>

የዚህ ክፍል ጊዜ ዓላማ ታሪኮችን በመተረክ በሽታዎች እንዴት ሊዛመቱ እንደሚችሉ ትምህርት መስጠት እንደሚቻል ማስገንዘብ ይሆናል። የትምህርቱ ጊዜ ካበቃ በኋላ ተሳታፊዎቹ በታሪኩ ፅንሠ ሀሳቦች ላይ በመንደርደር በሽታዎቹ የሚዛመቱበትን መንገዶችና መከላከያ ዘዴዎች መግለፅ ይኖርባቸዋል።

- የሚቀጥለውን ታሪክ ለተሳታፊዎቹ በማንበብ ዝንቦች እንዴት በሽታ እንደሚያዛምቱና የመተላለፊያውንም ሰንሰለት መንገድ እንዴት ማቋረጥ እንደሚቻል ውይይት ማካሄድ፣

- ለተሳታፊዎቹ አንድ 20 ደቂቃ በመስጠት ሌላ በአካባቢው የተለመደ ሁኔታ ላይ የተመረኮዘ የበሽታ መተላለፊያና መከላከያ ዘዴዎችን ያካተተ ታሪክ መተረክ ይችሉ እንደሆነ መጠየቅ።

<u>ታሪክ (ተረት)</u>

ከንጉሥ ሰለሞን የግዛት ዘመን በፊት በኢትዮጵያ ውስጥ ልዑል ነጋ የሚባል ኩሩና ሞኛሞኝ የሆነ ገዥ ይኖር ነበር። ይህም ልዑል በጣም አደን ይወዳል። እናም አንድ የአደን ቀን ጓደኛውን አብሮት ለአደን እንዲወጣ ሊጠይቀው ወሰነ። ጓደኛውም ዝንብ ነበር በዚያን ዘመን ዝንቦች ከሰው ልጅ ጋር ጥሩ ግንኙነት ነበራቸው።

በዚህም ጊዜ ዝንቡ በደስታ ጥያቄውን ተቀብሎ እቃውን በማዘጋጀት ጉዞአቸውን ወደ አደኑ ጫካ አመሩ። በመንገዳቸውም ላይ አንድ ትልቅ ፌቆ አዩ በዚህም ጊዜ አነጣጥሮ መምታት የዝንቡ ተራ ስለነበረ ሁሉቱም ሁኔታዎችን ለማጣራት ወደ ፌቆው ተጠጉ ዝንቡም አነጣጥሮ ጦሩን በመወርወር ገደለው ልዑሉም እሳት አያይዞው ሥጋውን ጠብሰው እንዲበሉና በነጋታው አደናቸውን እንዲቀጥሉ ሀሳብ አቀረበ። ዝንቡም ባለው የአደን ጥበብ ኩራት በጣም ተሰማው ከዛም የሚጠበሰውን ሥጋ ለማጣፈጥ አንዳንድ ጣዕም የሚሠጡ ፍራፍሬዎችን ልልቀም በማለት ወደ ጫካው ውስጥ ገባ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም ፍሬዎቹን ይዞ የሚጠበሰውን ሥጋ እያሰላሰለ ወደ ልዑሉ ጋ ተመለሠ። ግን አይኑን ማመን ያቃተው ሁኔታ ገጠመው ልዑሉም ወደ ዝንቡ ፊጥኖ በመጠጋት በመጠበስ ላይ ያለውን ሥጋ ከጫካ ውስጥ እነር ዘሎ በመውጣት እንደበላውና አጥንቱን ብቻ ጥሎ ጫካው እንደተመለሰ አስተዛዝኖ ነገረው። ዝንቡም በሁኔታው ተበሳጭቶ የሰበሰበውን ፍሬዎች መብላት ተያያዘ ልዑሉንም እንብላ ቢለው አይ አልበላም ምክንያቱም አነሩ ባደረገው ድርጊት በጣም ተበሳጭቻለሁ አለው። ዝንቡ ግን አባባሉ በጣም አስገረመው።

በነጋታው ጠዋት ተነስተው አደናቸውን ቀጠሉ በዚህ ጊዜ የማደኑ ተራ የልዑሉ ነበርና ወዲያው አንድ ጦጣ ባዩ ጊዜ አሸምቀው በመጠጋት ገደሏት ወዲያውም ርቧቸው ስለነበር እሳት አያይዘው መጥበስ ጀመሩ በዚህም ጊዜ ዝንቡ ምግባቸውን በተሻለ ሁኔታ ለማጣፈጥ እንዳለፈው ጊዜ ፍራፍሬዎችን ለመሰብሰብ ወደ ጫካ ውስጥ ገባ። ሲመለስ ግን ጥብሱም የለ ልዑሉም ተኝቷል። ወዲያው ልዑሉን ቀስቅሶ ስለ ሁኔታው ሲጠይቀው ጅብ መጥቶ እንደበላባቸውና ጅቡንም ብዙ እንዳሳደደውና ሥጋውን ለማስጣል እንደሞከረ ግን እንዳመለጠውና ደክሞትም እንደተኛ አወጋው።

ዝንቡም በነገሩ ተናደና አዝኖ ዐሐይ ከመጥለቋ በፊት ለሌላ አደን እንዲዘጋጁ ሀሳብ አቀረበና ተያይዘው ጉዞአቸውን ቀጠሉ ከጠቂት ሰዓታት በኋላ ድብ አዩና ዝንቡ አነጣጥሮ ገደለው። በጓደኛው ምክንያቶች በሙሉ ጥርጣሬ ውስጥ የገባው ዝንብም አንድ አይነት እውነታ ላይ መድረስ ስለፈለገ አሁንም በፈቃደኝነት ፍራፍሬ ለመሰብሰብ ወደ ጫካ ውስጥ ገባ ግን ተሸሽጎ ሁኔታዎችን ለመከታተል ስለፈለገ አንድ ዛፍ ጀርባ ተደበቀ ። እንደጠረጠረውም ልዑሉ የድቡን ሥጋ በአስቸኳይ ከጠበሰ በኋላ ጓደኛው ሳይመለስ መመገብ ጀመረ። ዝንቡም በጓደኛው አድራጎት በጣም አዝኖ ቀጥታ ወደ ቤቱ በረረ።

ለጥቂት ቀናት ያህል እቤቱ በመቀመጥ ንዴቱን ካበረደ በኋላ ሚስቱ አንድ ሀሳብ አቀረበች። ይኸውም በከተማው ውስጥ ያሉትን ዝንቦች ሁሉ ጠርቶ ስለሁኔታው እንዲያስረዳቸውና ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዲወሰኑ የሚል ነበር። የሚስቱንም ሀሳብ በመቀበል ስብሰባውን አዘጋጀ ስለሁኔታውም በዝርዝር ገለፃ አደረገላቸው። የሰው ልጅ ምን ያህል እራሱን እንደሚወድ በማስረዳት ይህንን ለመበቀል ምን ማድረግ እንዳለባቸው አንድ ሀሳብ አቀረበ ይኸውም የሰው ልጅ በአብዛኛው ምንም ስለንፅህና መሠረታዊ አጠባበቅ ስለማይጨነቅ የሚፀዳዳው ሜዳ ላይ ስለሆነ ማድረግ ያለብን የሚፀዳዳበት ሜዳ ላይ በሚገኘው ቆሻሻ (ዓይነ ምድር) ላይ ከተረማመድን በኋላ ተደብቀን በመሄድ በሚመገበው ምግብ ላይ በመንሸራሸር የለበለበነውን ቆሻሻ (ዓይነ ምድር) ምግቡ ውስጥ በማራገፍ የሰው ልጅ የራሱን ቆሻሻ (ዓይነ ምድር) መልሶ እንዲመገብ እናስደገድዳዋለን የሚል ነበር። በስብሰባውም ላይ የተገኙ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዝንቦች በሀሳቡ ውሳኔ በመስማማት ከዛንለት ጀምሮ አቅዱን ሥራ ላይ ማዋል ጀመሩ። የሰው ልጅም ልዑሉ ባጠፋው ጥፋት እስከ አሁን ድረስ ዝንቦች በሚያደርሱት የጤና ጠንቅ እየተሰቃየ በመኖር ላይ ይገኛል።

## ፩. የንፅህና ትምህርት እንቅስቃሴ - ትላልቅ ቡድን

### ፩ሀ. ፊልምና ቪዲዮ በመጠቀም

ፊልምና ቪዲዮ የማሳየት ዋናው ዓላማ አዳማጮን (ተመልካቹን) በማስደሰት (በማዝናናት) ትምህርት አዘል ሀሳቦችን ማስተላለፍ ነው። ፊልም ለማሳየት ፕሮጀክተር፣ ፊልም ማሳያ ጨርቅ (ስክሪን)፣ ጄነሬተር የመሳሰሉትን ቁሳቁሶች ማግኘት ውድና አስቸጋሪ ሲሆን ከውኃ ሀብት ሚኒስቴር ቢሮ ጋር በመነጋገር ማግኘት ይቻላል። በኢትዮጵያ ውስጥ ቪዲዮና የፊልም ክሮችን በመጠቀም የንፅህና ትምህርት ለመስጠት ሁለት አማራጮች ይኖራሉ እነሱም:-

- "የጤና መመሪያዎች" (ፕሪስክሪፕሽን ፎር ሔልዝ) በሚል ርዕስ በታይላንድ ውስጥ በዩኒሴፍ አማካይኘነት በቪዲዮና በፊልም ክሮች ላይ ተዘጋጅቶ የሚገኝ ሲሆን በአገራችንም የንፅህና ትምህርት ለማስተላለፍ የጎላ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። በእንግሊዝኛና በአማርኛ የተተረጎመ ቅጂ በአዲስ አበባ በዩኒሴፍ ቢሮ ይገኛል።

- "ቀላል ርምጃዎች ለተሻለ ጤና" (ሲምፕል ስቴፕስ ፎር ቤተር ሔልዝ) በሚል ርዕስ በመ.ው.ፍ.አ.ድ/ቯይካ የ11 ከተሞች የመጠጥ ውኃና የንፅህና ጥናት ቡድን የተዘጋጀ የቪዲዮ ፊልም ነው። በፊልሙም ውስጥ አግባብ በሌለው የንፅህና ሁኔታ የተነሳ የውኃ መገኛዎች፣ ማከፋፈያዎችና በቤትም ውስጥ ውኃ እንዴት በንፅህና ጉድለት የተነሳ ለብክለት እንደሚጋለጥና መከላከያ ዘዴዎቹም ምን እንደሆኑ ግንዛቤዎችን የሚያስጨብጥ ሲሆን ባጠቃላይ የውኃና ንፅህና ግንኙነት ሁኔታን ይጠቁማል። የቪዲዮዎቹም ቅጂ በአማርኛ፣ አፋርኛና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች ተዘጋጅቶ በውኃ ሀብት ሚኒስቴር መ/ቤት ውስጥ ይገኛል።

  - ትምህርታዊ ቪዲዮም ሆነ ፊልም ለማሳየት ቦታ መምረጥ ያስፈልጋል ይኸውም ፊልም በአንድ ጊዜ ለብዙ ሰዎች ማሳየት ይቻላል። እንደ አየሩ ሁኔታ ከቤት ውጭ ማታ ቢሆን ይመረጣል። ቪዲዮ ግን ቤት ውስጥ ማታ ወይም ቀን ሊታይ ይችላል ተመልካቹ በአንድ ጊዜ ከ30 ሰው ያልበለጠ ቢሆን ይመረጣል።

  - ድምፅ ማጉያ ወይም ማስታወቂያ መለጠፊያ ቦርድ በመጠቀም ቅስቀሳ በማድረግና ከሚመለከተው ባለሥልጣን ትምህርታዊ ቪዲዮውን ወይም ፊልሙን ለማሳየት ፍቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።

  - ስለ ፊልሙ ወይም ቪዲዮው መልእክት ተጨማሪ ፍሬ ሀሳቦችን መግለፅ ካስፈለገ ከመጀመሩ በፊት ቢሆን ይመረጣል፣

- ፊልሙ ወይም ቪዲዮው ካለቀ በኋላ ሕዝቡን ማሰናበት ይገባል። ምክንያቱም አዳማጪው (ተመልካቹ) በስተመጨረሻ ውይይት ይኖራል ቢባል የመሰልቸት ሁኔታ ላይ ሊደረስ ይችላል። አስፈላጊ ከሆነ የተወሰኑ ሰዎች በማለቂያው ላይ በመጋበዝ ፍሬ ሀሳቦችን መለዋወጥ ይችላል።

6ለ. <u>የመንገድ ላይ ትርዒት መጠቀም (በድራማ መልክና አሻንጉሊቶች በማሳየት)</u>

አንዳንድ ትርዒት በሰፈር ውስጥ አመቺ ቦታ ላይ በማዘጋጀት የንፅህና ትምህርት መልዕክቶችን ማስተላለፍ ይቻላል። ትርዒቱ አጠር ያለና ቀለል ያለ ታሪክ ያካተተ የተመልካቾችን አስተሳሰብ የሚስብና ትምህርት አዘል አዝናኝ መሆን ይኖርበታል። የመንገድ ላይ ትርዒት ለማዘጋጀት፦

- እያንዳንዱ ትርዒቱ ዝግጅት ላይ የሚሳተፍ ግለሰብ የትርዒቱን ዓላማ በደንብ የተገነዘበ መሆን አለበት። የተለያየ ሙያ ያላቸውንና በአብዛኛው ከንፅህና ጉድለት ጋር ተዛምዶ በሚከሰት በሽታ የሚጠቃ የኅብረተሰቡን ክፍል በመጋበዝ ትርዒቱ ምን ያህል ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር እንደሚዛመድ መገመት ይቻላል፣

- ቀደም ብሎ በድራማ፣ ዘፈን ወይም የአሻንጉሊት ትርዒት በመጠቀም ትምህርት ያዘጋጁ ድርጅቶች (ክፍሎች) በአካባቢ ካሉ ልምድ መለዋወጥ ይጠቅማል፣

- እያንዳንዱ ድራማ ቢበዛ ከ10 ደቂቃ መብለጥ የለበትም። በተቻለ መጠን ተመልካቹ መልዕክቱን ማዳመጥ እንዲችል ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል፣

- በአሻንጉሊቶች መልክ ትርዒት እንዲዘጋጅ ከተወሰነ አስፈላጊውን መልዕክት ሊያስተላልፉ የሚችሉ አሻንጉሊቶችን መሰብሰብ፣

- ሥራዎችን በቅድሚያ መከፋፈል <u>ለምሳሌ</u>፦ አስተዋዋቂ፣ ጥያቄዎችን የሚጠይቅ ወዘተ…፣

- ከትርዒቱ ጋር የሚዛመዱ መልዕክቶችን ያካተተ ባሕላዊ ዘፈን ማዘጋጀት፣

- ትርዒቱን ለኅብረተሰቡ ከማቅረብ በፊት ልምምድ ካማካሄድ ማሻሻያ ሀሳቦች ካሉ ለማስተካከል መሞከር፣

**ትርዒቱ ለሕዝብ ዕይታ በሚቀርብበት ወቅት**

- በከተማው ውስጥ የሚገኙ ድርጅቶችን መጋበዝ ለምሳሌ:- አስተማሪዎች፣ የሕክምና ቤት ሠራተኞች፣ የውኃ ክፍል ሠራተኞች፣ የንግድ ተጠሪዎች ወዘተ...፣

- ሕዝቡ ከተሰበሰበና የተዘጋጀለትን ቦታ (መቀመጫ) እስኪይዝ ድረስ ዘፈን ማሰማት፣

- ትርዒቱ ሊጀመር እንደሆነ ማስገንዘብ፣ በትርዒቱ መካከል ተመልካቹ ፀጥ እስኪል ድረስ መልዕክት ለማስተላለፍ (ትርዒቱን ለመቀጠል) አለመቸኮል፣

- በትርዒቱ መጨረሻ አንዳንድ ጥያቄዎችን መጠየቅና ትክክለኛውን የትርዒቱን ፍሬ ሀሳብ ለአዳማጩ ደግሞ ለማስገንዘብ መሞከር፣ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ተቀባይነት ማግኘቱን ማረጋገጥ፣

- በመጠጨረሻም ተመልካቹን በማመስገን መሰናበት።




## <u>በትምህርቱ ወቅት መደረግና መወገድ ያለበት ሁኔታ</u>

### *መደረግ ያለበት ሁኔታ*

- ወንድ የሴት ልብስ መልበስ፣
- ትክክለኛ ምሳሌ ሊሆን የሚችል አስቂኝ የሰፈር ገጠመኝ ምሳሌ፡- የስካር ሁኔታ፣ ልመና፣ የቤት ሠራተኛ አባባል (ዘይቤ)፣ የልምድ መድኃኒተኛ፣ አጭበርባሪ ነጋዴ ወዘተ…፣
- የተጋነነ በህሪያት፣
- አስፈሪ ሁኔታዎች ምሳሌ፡- ሞት፣ የሙት መንፈስ እንቅስቃሴ፣ ወዘተ…፣
- ዘፈንና ጭፈራ፣
- አዳማጮችን ጥያቄ መጠየቅና መልስ ማግኘት፣
- አነስና ቀለል ያሉ መልዕክቶች ለማስተላለፍ መሞከር፣
- በእንቅስቃሴ ላይ የተመረኮዘ መልዕክት፣
- የአዳማጮች ተሳትፎ፣
- የሚታይና ቅዕበታዊ የሆነ ባህርይ፣

### *መወገድ ያለበት*

- በአይታዎች መካከል የሚፈጠር ረጅም ሠንት፣
- ፈጣን ንግግር፣
- በአንድ ጊዜ ከአንድ ሰው በላይ መናገር፣



- ተቀምጦ ወይም ተኝቶ ትርዒት ማቅረብ፣

- አንድ የትርዒት አቅራቢ ብቻ እንቅስቃሴ የሌለበት ረጅም ገለፃ ማድረግ፣

- የተለያዩ የቲያትሩን መልዕክቶች አንድ ግለሰብ ብቻ ማቅረብ (መጫወት)፣

- ውስብስብ የሆኑ እቅዶችና ገላፃዎች፣

<u>በአሻንጉሊት ትርዒት ዕይታ ወቅት መደረግና መወገድ ያለበት ሁኔታ</u>

*መደረግ ያለበት ሁኔታ*

- ቀላልና አጠር ያለ ዕቅድ ማውጣት፣

- የእንስሳት ባሕርይያትን መናገር ለምሳሌ፡- ዝንብ፣ ትል፣ ቅማል፣ ወዘተ...፣

- በአሻንጉሊቶች መሀከል የሚካሄዱ ሁኔታዎች ለምሳሌ፡- መደባደብ፣ እንዱ አንዱን መሸከም፣ ዘለፋ፣ ወዘተ...፣ (አብዛኛውን ጊዜ ሰው ሊያቀርበው የማይቻለው ሁኔታዎች)

- በእይታዎች መካከል ፈጣን የሆነ ለውጥ፣

- መሰማት የሚችልና ዝግ ያለ ንግግር፣

- በአንድ ጊዜ በእንቅስቃሴ የተደገፈ አንድ ባሕርያትን ብቻ መናገር፣

- ዘፈንና ጭፈራ፣

- አስቂኝ የሆነ የድርጊት ድምፅ ማሰማት ምሳሌ፡- ሕፃን ልጅ (ሰው) ሲፅዳዳ

*መወገድ ያለበት*

- በአንድ አሻንጉሊት ብቻ ረጅም የእይታ ጊዜ፣

- የአሻንጉሊቶች እንቅስቃሴ ሳይኖር በድምፅ ብቻ መልዕክት ማስተላለፍ፣

- አሻንጉሊቶቹ በእይታ መሀል አዳማጩን ጥያቄ መጠየቅ፣

## 7. <u>ልጅ-ለልጅ ዓይነት አቀራረብ</u>

ሕፃናት አብዛኛውን ጊዜ ከወላጆቻቸው ጋር ጊዜን ከማሳለፍ ይልቅ ከታላቅ እህቶቻቸውና ወንድሞቻቸው ጋር መሆንን ይመርጣሉ። በእድሜ ከፍ ያሉ ሕፃናትም ታናናሾቻቸውን መንከባከብ ያስደስታቸዋል። ምክንያቱም ትልቅነት ይሰማቸዋልና። በዚህም ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ ከፍ ከፍ ያሉ ሕፃናትን የታናናሾቻቸውን ጤና እንዴት መንከባከብ እንደሚችሉ ትምህርት ቢሰጣቸው አመርቂ የሆኑ ክንውኖችን በኅብረተሰቡ አስተሳሰብ ዘንድ ሊያሠርፁ ይችላሉ።

- ልጆች ጤናን በሚመለከት ሥራ በተቀዳሚነት የሚቀርቡ ብቻ ሳይሆኑ የጤና እንክብካቤ ሂደት መነሻ ይሆናሉ፣

- ልጆች ስለ ጤና አጠባበቅ በተጨባጭ ሁኔታ ተምረው ካደጉ ለወደፊቱ ጤናን በሚመለከት የተሻለ የቤተሰብ ኃላፊ ይሆናሉ፣

- ልጅ-ለልጅ ዓይነት መልዕክት ማስተላለፍፊያ መንገድ በትምህርት ቤት ውስጥ ነፃ የሆነ ትምህርታዊ ዘዴ ሊሆን ሲችል በልጆቻቸው አማካኝነትም ለወላጆች ትምህርቱ ሊተላለፍ ይችላል፣

- ልጆች እርስ በእርስ ሀሳብን በመለዋወጥ ያላቸውን ዕውቀት ሊያዳብሩና ሁኔታዎችን ሊቀይሩ ይችላሉ፣

- ይህ ልጅ-ለልጅ ትምህርታዊ መልዕክቶችን ማስተላለፊያ ዘዴ የተነደፈው ልጆችን በቤተሰብ የጤና ሁኔታ ላይ ትልቅ የኃላፊነት ሚና እንደሚጫወቱ በማመን ነው። ይህ ዘዴ ልጆች በልምድ ውስጥ በማለፍ ትምህርትን እንዲቀስሙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ለችግሮችም በራሳቸው ጥረት መፍትሄ እንዲፈልጉና አርቀው እንዲያስቡ ሲያደርግ ትምህርትን በጭንቅ ሳይሆን በጨዋታና በቀልድ መልክ እንዲቀበሉና በራስ ላይ የመተማመን ሁኔታዎችንም ያመቻቻል።

ትምህርቱን ለማካሄድ መወሰድ ያለባቸው ደረጃዎች፣

- ከወላጆች ወይም ከሚመለከታቸው ግለሰቦች ፍቃድ በመጠየቅ፤ የሰንት ጉዳይ፣ መከተት ያለበትን ነጥብ፣ የሰራውን ሁኔታ፣ ወዘተ... ማመቻቸት፣

- በልጆች መሀከል መተባበርና ሀሳብ መለዋወጥን ለማጎልበት ጨዋታዎችን፣ ሥዕሎችን፣ ውይይቶችን፣ ወዘተ... የመሳሰሉ ዝግጅቶችን ማስተባበር፣

- በሚዘጋጀው የትምህርት ርዕስ ላይ የተመሠረተ ሰፋ ያለ ውይይት እንዲካሄድ ማድረግ፣

- ተሳታፊዎችን በፍላጎታቸው ላይ የተመሠረተ ቡድን እንዲያቋቁሙ በማድረግ ከቡድናቸው ርዕስ ጋር ግንኙነት ያለው መረጃ በማሰባሰብ ውይይት እንዲያካሂዱ መጠየቅ። ለምሳሌ፦ በአንድ አካባቢ ስለተከሰተ የተቅማጥ ወረርሽኝ ከተለያዩ የንፅህና ሁኔታዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ወይም ወቅታዊ የሆነ የተቅማጥ በሽታ መንስዔ የመሳሰሉትን፣

- በቡድኖች መሐከል በተሰበሰቡት መረጃዎች ላይ ውይይት በማካሄድ የአቀራረብ ዕውቀትን ማዳበር፣

- በአዳማጮች የአስተሳሰብ ሁኔታ ላይ የተመረኮዘ የአቀራረብ ዘዴዎችን መቀየስ። ለምሳሌ፦ ለወላጆች፣ ለልጆች፣ ወዘተ... የሚቀርብ፣

- ትምህርቱን የሚያስተላልፉ ተሳታፊዎች መልዕክታቸውን የሚያስተላልፉበት የአሻንጉሊት ትርዒት፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ፖስተሮች፣ ወዘተ... እንዲያዘጋጁ ማድረግ፣

- ተሳታፊዎቹ የትምህርቱን ግብ መምታት ወይም ተቀባይነት ማጣት እንዲገመግሙ ማድረግ።

ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች በመከተል በተለያየ የእድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ ልጆች ለታላላቆቻቸው ወይም ለታናናሾቻቸው መልዕክትን በማስተላለፍ ሁኔታዎችን ሊያመቻቹ ሲችሉ ለራሳቸውም ጠንካራ የሆነ በራስ ላይ መተማመን ሊያሳድሩ ይችላሉ።


8. <u>የሁኔታዎችን ለውጥ መቆጣጠር</u>

ቁጥጥርና ግምገማ የታቀዱ ሥራዎች በተገቢው መንገድ ምን ያህል ተፈጻሚ እንደሆኑና ተቀባይነት እንዳላቸው ለማወቅ የሚረዱ ዘዴዎች ናቸው።

ማንኛውም ዓይነት ኅብረተሰብ ዕድገት ዕቅድ ዋና ዓላማ የኅብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታ ጥራት መለወጥ ሲሆን (ለምሳሌ:- የንፅህና ትምህርት ዕቅድ በማውጣት የአንድ አካባቢን የኑሮ ሁኔታ በመለወጥ የኅብረተሰቡን ጤና እስተማማኝ ማድረግ) ለዚህም ብዙ የለውጥ ሂደቶችን ማካሄድ ይጠይቃል። የኅብረተሰቡን ጤና የሚያውኩ የተለያዩ ሁኔታዎች ስላሉ አላማና ግቡን በማመዛዘን ዝርዝር እርን ማየቱ ይጠቅማል። ሽንት ቤት ማስቆፈር ምናልባት ጤናን ለማሻሻል ዋና አላማ ተደርጎ ቢታሰብ ግን አላማው ግቡን በዚህ ብቻ ሊመታ ይችላል? ስለዚህ የታሰበው ዓላማ የተቆፈረውን ሽንት ቤት በንፅህና ይዞ መጠቀም ምናልባት ዓላማውን ግብታዊ ሊያደርገው ይችላል። በተጨማሪም ኅብረተሰቡ ሽንት ቤት ስለ ማስፈለጉና በንፅህና መያዝና በአግባቡ መጠቀምም እንዳለበት ግንዛቤ እንዲያገኝ ካልተደረገ የተሠራው ሽንት ቤት ጠቄሜታ አይሰጥም። ስለዚህም ለሚሰሩ እንቅስቃሴዎች ዕቅድ፣ ክትትልና ግምገማ ማካሄድ ይገባል። ጠቋሚ ድርጊቶችን በመከታተል የሁኔታዎች ለውጥ መኖሩንና የታቀደውም ዓላማ ላይ መደረሱን መገንዘብ ይቻላል።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ለምሳሌ:- | ዓላማ | - | የሕፃናትን አይነምድር በንፅህና ሁኔታ መወገድ |
| | ጠቋሚ እንቅስቃሴዎች (ድርጊቶች) | - | በግቢ ውስጥ የሕፃናት አይነምድር ያለማግኘት ልጆች ሽንት ቤትን በአግባቡ ሲጠቀሙ መመልከት እናቶች የልጆችን አይነምድር በተገቢው መንገድ ለማስወገድ ያላቸው ግንዛቤ |

ክትትልና ግምገማ ለማካሄድ የሚሰበሰቡ ሀሳቦች ልክ መሠረታዊ የሆኑ ሀሳቦችን ለማሰባሰብ በሚጠቅም ዘዴ ላይ በመመርኮዝ ሊካሄድ ይችላል። ይኸም ዘዴ የማያቋርጥ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ሲወክል የንፅህና ትምህርት አሰጣጥንም በተሻለ ሁኔታ ግብታዊ ያደርጋል።


መለካት፤
መገምገም
ለምን አስፈለገ?

8ሀ. *<u>ራስን መመዘኛ ቅጽ</u> (የመገምገሚያና የመከታተያ ቅፅ)*

የዚህ ክፍለጊዜ ዋና ዓላማ ኅብረተሰቡን ባካባቢው ያሉ ጠቃሚ መረጃዎችን በማሰባሰብ ሁኔታ ላይ በማሳተፍ፤ በቀላሉ የንፅህና ሁኔታ ማሻሻያ እንቅስቃሴዎች ላይ እንዲደርስ እገዛ ለማድረግ ነው፡፡ የዚህ ክፍለጊዜ ትምህርት በተለያዩ የተሳታፊዎቹ ሥልጠና ጊዜያት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡፡

- ለተሳታፊዎቹ ከሥልጠናቸው ምን ያህል እንደተማሩ ጥያቄ ማቅረብ፡፡ ለምሳሌ፡- በየግል ቤታቸው ውስጥ መቀየር ያለበት ልምድ (እንቅስቃሴ) ይኖራል ብለው ይገምታሉ?




- በሥልጠናው ውጤት መሠረት በአካባቢያቸው ላይ ለውጥ መኖሩን እንዴት ሊያውቁ እንደሚችሉ መጠየቅ፡፡ እንዴትስ የሁኔታዎች ለውጥ ምልክት እንዳለ ሊያውቁ ይችላሉ?

- በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ለእያንዳንዱ ግለሰብ የራስ መመዘኛ ቅፅ በመስጠት በቤተሰቡ ውስጥ የሚካሄደውን የንፅህና ሁኔታ እንዲሞላ መጠየቅ በእያንዳንዱ ቅፅ ላይ የተሞላው ሁኔታ ሁሉ የቤተሰቡ አባላት በሙሉ የተስማሙበት መሆኑን ማረጋገጥ፣

- አንድ ጠቃሚ የሆነ ባሕሪ በምን ዓይነት የምዝገባ ዘዴ መመዝገብ እንዳለበትና ለምን ያህል ጊዜም ክትትል ሊደረግለት እንደሚገባ ከቤተሰቡ አባላት ጋር በመሆን መወሰን፡፡

የሥልጠና አሰጣጥ ዘዴዎች መገምገም ሲኖርባቸው የሥልጠናው አቀራረብና ይዞታ ማሻሻያ ያስፈልጋቸው እንደሆነ ተመዝግበው መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ በክፍል ሦስት ላይ የቀረቡት የግምገማ ገፀባህርያት ከእያንዳንዱ የሥልጠና ክፍለጊዜያት በኋላ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡ ተሳታፊዎችም አጢነው በመመልከት የትኛው ገፀባህርያት የሥልጠናውን መልዕክት እንደሚያንፀባርቅ እንዲገልፁ መጋበዝ፡፡ እያንዳንዱ ገፀባህርያት ምን ዓይነት ትርጉም እንዳለው (እንደሚሰጥ) ከቡድኑ ጋር በመጀመሪያ በመወያየት አንድ ዓይነት ውሳኔ ላይ መድረስ ያስፈልጋል፡፡

የመገምገሚያና የመከታተያ ቅጽ

| ተግባራት | አንደኛ ወር | ሁለተኛ ወር | ሦስተኛ ወር |
|---|---|---|---|
|  | | | |
|  | | | |
|  | | | |
|  | | | |
|  | | | |
|  | | | |
|  | | | |

9. <u>በኢትዮጵያ ውስጥ በንፅህና አጠባበቅ ትምህርት ላይ የሚሳተፉ ድርጅቶች</u>

- የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
- የትምህርት ሚኒስቴር
- የግብርና ሚኒስቴር
- ዓለም አቀፍ የሕፃናት መርጃ ድርጅት (ዩኒሴፍ)
- ኦክስፋም
- ዋተር ኤድ
- የፊንላንድ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (ፊኒዳ)

## 10. ሌሎች ጠቃሚ ፅሑፎች


1. Water Born diseases and Their Preventation UNESCO (No Date), Ministry of Health

2. Environmental Health, 1986, Ministry of Health

3. Community Health Directives, 1988, Ministry of Health

4. Health Care Education and Instruction, 1991, Ministry of Health

5. Methods of Prevention, Vaccination and Diarrhea, (No Date), Ministry of Health

## ይህንን መመሪያ ለማዘጋጀት እንደመንደርደሪያ የተጠቀምንባቸው ፅሑፎች

"Making the Links"
Guidelines for Hygiene Education in Community Water Supply
IRC Occasional Paper series, No. 5

The Copy Book
Copyright-Free Illustrations for Development,
Intermediate Technology, 1991

Oasis Partnership Supplement
Water Aid, 1993

Wealth Ranking in Smallholder Communities: A field Manual
Barbara E Grandin, Intermediate Technology Publications, 1998

Education for Better Health
A manual for Senior Health Educators
Reidulf K. Molvaer,
UNICEF/Ministry of Health, Addis Ababa, 1989

The Hygiene Education Training Manual for Community Use
Suzanne Ferron
British Council, Nigeria, 1995

Actions Speak
The Study of Hygiene Behaviour in Water and Sanitation Projects
ODA/WHO/UNDP/IRC/London School of Hygiene and Tropical Medicine, 1993

Tools for Community Participation
A Manual for Training Trainers in Participatory Techniques
Lyra Srinivasan
PROWESS/UNDP Technical Series
Involving Women in Water and Sanitation, 1990

Children for Health
Children as Communicators of Facts for Life
Child-to-Child Trust/UNICEF, 1993

Helping Health Workers Learn
David Werner and Bill Bower,
The Hesperian Foundation, 1991

Just Stir Gently


The way to mix hygiene education with water supply and sanitation
IRC Technical Paper Series No. 29, 1991

# ሌሎች ለምሳሌ የሚሆኑ ስዕሎች





















SOAP

























JICA

LIB